# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 297 ሰኔ 27 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


ከ455 ሺህ በላይ መጻህፍት ተሰብስቧል

## አብርኆት ቤተ መጻህፍትን ለማቋቋም ተሳትፎ ላደረጉ ተቋማትና ግለሰቦች ምስጋና ቀረበ



ፎቶ - በገባቦ ገብሬ

አዲስ አበባ፡- የአብርኆት ቤተ መጻህፍት ከራሱ አልፎ ለሌሎች ሊለግስ በሚችል ቁመና ላይ እንዲደርስ በአገር ውስጥና በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድርጋቸውን በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት የማህበራዊ ዘርፍ አማካሪ ሙአዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ገለጹ።

የመጀመሪያ ምእራፍ የመጻህፍት ማሰባሰቢያ መርሃ ግብር ማጠናቀቂያ ላይ ሙአዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል እንደገለጹት፤ ቤተ መጻህፍቱን ከሕዝብ ጋር የማገናኘት ሂደቱ በስኬት ቢጠናቀቅም፤ መጽሃፍ መቀበልና መስጠት ባህል ሆኖ ሊቀጥል ይገባል፡፡

አብርኆት ወጣቱ እውቀት የሚገበይበት ስፍራ እንዲኖረው ማስቻሉን የጠቆሙት ሙአዘጥበባት ዲያቆን ዳንኤል፤ እንዲህ አይነት ተቋም ድንጋይ የሚወረውር፣ እርስ በእርሱ የሚጋጭ፣ በዘር የሚከፋፈል፣ በፖለቲካ አመለካከት የግጭት መነሻ ነው ብሎ የሚያስብ ትውልድ እንዳይኖር ከማድረግ ባለፈ በውይይትና በክርክር

አብርኆት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - በገባቦ ገብሬ

ኢንጅነር ግደይ ዘርአፅዮን

## ሕወሓት ትንኮሳውን አቁሞ ለሰላም ዝግጁ እንዲሆን ጥሪ ቀረበ

ማእረግ ገ/እግዚአብሔር

አዲስ አበባ፡- በሰሜን ያለው ግጭት እንዲያበቃና የትግራይ ሕዝብ ዘላቂ ሰላም እንዲያገኝ ሕወሓት ትንኮሳውን አቁሞ ወደሰላም መመለስ እንዳለበት ተገለጸ። መንግሥት የሰጠውን ተደጋጋሚ የሰላም እድል ሕወሓት ሊጠቀምበት እንደሚገባም አሳስበዋል፡፡

ሕወሓት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ፕሮጀክቱ የኦሮሚያ ልዩ ዞንና የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችን ይበልጥ የሚያስተሳስር ድልድይ መሆኑ ተገለጸ

### - የለገዳዲ ምዕራፍ ሁለት የከርሰምድር የውሃ ፕሮጀክት ተመረቀ

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- የለገዳዲ ምዕራፍ ሁለት የከርሰ ምድር የውሃ ፕሮጀክት የኦሮሚያ ልዩ ዞንና የአዲስ አበባን ከተማ ነዋሪዎችን ይበልጥ የሚያስተሳስር ድልድይ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ፡፡

በትናንትናው ዕለት በተመረቀው የለገዳዲ ምዕራፍ ሁለት የከርሰ ምድር የውሃ ፕሮጀክት ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደገለጹት፤ የውሃው ፕሮጀክት የኦሮሚያ ልዩ ዞንና የአዲስ አበባን ከተማ ነዋሪዎች ይበልጥ የሚያስተሳስር ድልድይ ነው፡፡ ከንቲባ አዳነች እንደገለጹት፤ የአዲስ አበባ ሕዝብና በአዲስ አበባ አጎራባች ያለው የኦሮሚያ ሕዝብ ፈጽሞ መነጣጠል አይችልም፡፡ ወደፊትም በመተባበር፣ በመዋደድ፤ በአብሮነትና በመተሳሰብ የጋራ እሴቱን በማሳደግ መኖር ይጠበቅበታል፡፡

የአዲስ አበባና የኦሮሚያ አጎራባች ሕዝቦች አንዱ ለሌላው መኖር ምክንያት ከመሆኑም ባሻገር፣ አንዱ ያለ ሌላው መኖር አይችሉም ያሉት ከንቲባዋ፤ የልማት ስራዎች ሲሰሩ የጋራ ተጠቃሚነትን ታሳቢ ያደረገና የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን የሚያጠናክር መሆን አለበት ብለዋል፡፡

ሊነጣጠል የማይችል መሰረታዊ ግንኙነታውን የማያውቁና የግል ፍላጎታቸውን መተግበር የሚፈልጉ አካላት ሕዝቡን የሚያስከፋ ሃሳብን ከማስተላለፍ መቆጠብ እንዳባቸውም ከንቲባ አዳነች አስገንዝበዋል፡፡

አዲስ አበባ 85 በመቶ የውሃ ፍጆታዋን የምታገኘው ከኦሮሚያ አጎራባች ዞኖች መሆኑን የገለጹት ከንቲባዋ፤ ፕሮጀክቱ በሚለማበት አካባቢ ነዋሪዎችን ውሃ



ፎቶ - ዳኜ አበራ

ሰጥተውን ውሃ እንዲጠማቸው የሚያደርግ ሳይሆን የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት ብለዋል፡፡

ከንቲባ አዳነች እንደገለጹት፤ አንዳንድ ፖለቲከኞች የሕዝቡን ቅሬታ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ለፖለቲካ ፍላጎታቸው ሲጠቀሙበት ይስተዋላሉ፡፡ ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን በማረጋገጥ በኩል ፕሮጀክቱ ችግር የቀረፈ ነው፡፡ በለገዳዲ ክፍል ሁለት ፕሮጀክት ብቻ ıı የሚደርሱ የውሃ ፕሮጀክቶች ለአካባቢ ሕዝብ ማቅረብ ተችሏል፤ አዳዲስ ፕሮጀክቶች በሚሰሩባቸው አካባቢዎች በድምሩ ወደ 30 የሚደርሱ የውሃ ጉድጓዶች ለሕዝብ ማቅረብ መቻሉንም ገልጸዋል፡፡

እንደ ከንቲባ አዳነች ገለጻ፤ ፕሮጀክቱ የአዲስ አበባን የውሃ አቅርቦት ችግርን የሚፈታ ነው፡፡ በተለይ የጉለሌንና የየካ ክፍለ ከተማ ነዋሪዎችን የውሃ ችግር ይፈታል፡፡ በቀን ከ86 ሺህ ሜትሪክ ኪዩቢክ በላይ የከርሰ ምድርን ውሃ በማምረት ከ860 ሺህ በላይ ለሆኑ የከተማ ነዋሪዎች በቀጥታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያስችላል፡፡ በአዲስ ታሪክ

ፕሮጀክቱ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## “ከወዳጅነት ጠላትነትን፣ ከልማት ጥፋትን ማጉላት የግል አመለካከት እንጂ የሚዲያ ተግባር አይደለም”

-አቶ መሐመድ አህመድ
በኦሮሚያ ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት የባህልና ሚዲያ ጉዳዮች አማካሪ

ገጽ 4







በአንድ አይነት ግጥም እና ዜማ ስለሀገራችን የምንዘምርበት ጊዜ ላይ ነን!

ገጽ 7

‹‹በስተጀርባ ያለው ኃይል እየተዳከመ ከመጣ አሸባሪው ሸኔ ቦታ አይኖረውም››

- ዶክተር ዲማ ነገዎ

ገጽ 10

ዜና

# ዩኒቨርሲቲው ውጤታማ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን ገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ በተመደበበት የ‹‹ተግባር ተኮር›› ዘርፍ ለአገር ከፍተኛ አበርክቶ ያላቸውን የጥናትና ምርምር ስራዎች እያከናወነ መሆኑን አስታወቀ፡፡

የደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ንጉስ ታደሰ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ በጥናት ተለይቶ የተግባር ተኮር ዩኒቨርሲቲ መሆኑ በተወሰኑ የትምህርት ዘርፎች አተኩሮ ጥናትና ምርምር በማካሄድ ውጤታማ ስራ እየሰራ ነው፡፡

እንደ ዶክተር ንጉስ ገለጻ፤ ከዚህ በፊት በሁሉም ዘርፍ ምርምር ይደረጋል፤ ነገር ግን የሰው ኃይልና የገንዘብ እጥረት የሚገጥም በመሆኑ ከመነካካት ያለፈ ውጤት አይመጣም፡፡

ዩኒቨርሲቲው ተግባር ተኮር መሆኑን ተከትሎ የአካባቢውን ችግር ሊቀርፉ የሚችሉ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድ ለአገር የሚጠቅም ስራ እየሰራ ነው ያሉት ዶክተር ንጉስ፤ ሕብረተሰቡ እንዲፈቱለት የፈልጋቸውን ችግሮች በመለየት በጥናት ተደገፈ መፍትሔ እንድንሰጥ አስችሎናል ብለዋል፡፡

እንደ ዶክተር ንጉስ ገለጻ፤ ከማሕበረሰቡ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ከጤና፣ ከግብርና፣ ከኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ ጋር የተገናኙ ጥናቶች በስፋት እያካሄድን ነው ያሉት ዶክተር ንጉስ፤ በጤናው ዘርፍ ሕብረተሰቡ ጋር ያለውን እውቀት በመዘናዊ አሰራር በመደገፍ ተደራሽነቱ እንዲሰፋና የእውቀት ሽግግር እንዲኖር በትኩረት እየተሰራ ነው።

ተግባር ተኮር መሆናችን ከዚህ ቀደም እንደነበረው በብዙ የትምህርት መስክ ጥናት ለማድረግ ከመሞከር በተወሰኑ የትምህርት መስኮች ላይ በትኩረት በመስራት ውጤት ለማምጣት እየረዳን ነው ያሉት ዶክተር ንጉስ፤ እንዲሁም ያለንን ውስን የሰው ኃይልና የገንዘብ ሀብታችንን በሥርዓት ለመጠቀም ከፍተኛ



ዶክተር ንጉስ ታደሰ

እድል እንደፈጠረላቸው ገልጸዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው የተግባር ተኮር የተባለው አካባቢውና ዓለም አቀፍ ጠቀሜታው ታይቶ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ የሆነ የኢንቨስትመንት አቅም በመኖሩ በኢንጂነሪን ዘርፍ ከፍተኛ ስራ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

የሚሰጡ ትምህርቶችንም ከ ኢ ን ቨ ስ ት መ ን ት ና ከኢንዱስትሪ ጋር አስተሳስረን የተግባር ትምህርት ለተማሪዎች በመስጠት በተለያዩ መስኮች ኢንቨስት የሚያደርጉ ባለሀብቶችም ተጠቃሚ እየሆኑ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ዩኒቨርሲቲው በተግባር ተኮር ዘርፍ ከተመደበ ጊዜ ጀምሮ የአካባቢውን አቅም በጥናትና ምርምር ለይቶ በማጉላት ሕብረተሰቡን ይበልጥ ተጠቃሚ የሚያደርጉ ስራዎችን እንዲሰራ አስችሎታል ብለዋል፡፡

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ ተማሪዎች ተመርቀው ወደ ኢንዱስትሪዎች በሚቀላቀሉበት ጊዜ በቀጥታ ወደ ስራ እንዲገቡ የሚያስችል የተግባር እውቀት እንዲኖራቸው እየተደረገ ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች በተግባር የበለጸጉና ልምድ ያላቸው ሆነው እንዲወጡ በማድረግ ወደ ስራ ዓለም ሲቀላቀሉ ችግር የሚቀርፉና በራሳቸው መስራት የሚችሉ እንዲሆኑ አስፈላጊው የተግባር ትምህርት እየተሰጠ መሆኑንና አካባቢው የኢንዱስትሪ መንደር በመሆኑ መማር ማስተማሩ ተግባር ተኮር እንዲሆን በዋናነት እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

# የሀገራችንን እድገትና ክብር ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ሰላማችንን ጠብቀን በትጋት እንድንሠራ ተጠየቀ

**ኢያሱ መሰለ**

አርባ ምንጭ፡- ኢትዮጵያውያን በመቻቻልና በመተባበር ሰላማችንን ጠብቅን ጊዜንና ቴክኖሎጂን በአግባቡ በመጠቀም በትጋት ከሰራን የሀገራችንን እድገትና ክብር ወደ ላቀ ደረጃ ማድረስ እንችላለን ሲሉ የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ተናገሩ።

የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ባሳለፍነው ቅዳሜ ለ35ኛ ጊዜ ተማሪዎችን ባስመቀረበት ወቅት የዩኒቨርሲው ፕሬዚዳንት ዶክተር ዳምጠው ዳርዛ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ በሀገሪቱ የሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድርሻቸው የጐላ ነው፡፡

ተመራቂዎች በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ በቆዩባቸው ዓመታት ሰላምን ለማደፍረስ ከሩቅ የሚሰራጩ እኩይ ተልእኮዎችን ባለማስተናገድ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በፍቅር የሚኖርባት ትንሿ ኢትዮጵያ የመሆኗን ባህል አጥንክረው የወጡ መሆናቸውን የተናገሩት ፕሬዚዳንቱ፤ መልካም ስነምግባራቸውን በማስቀጠል በሚሄዱበት አካባቢ ሁሉ ለኢትዮጵያ ሰላም ፣ ልማትና ዴሞክራሲ ቅድሚያ ሰጥተው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ አሳስበዋል።

አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ በ1979 ዓ.ም በውሃ ቴክኖሎጂ በኢንስቲትዩት ደረጃ ተቋቁሞ ስራ እንደጀመረ የገለጹት ፕሬዘዳንቱ፣ በ1996 ዓ.ም ወደ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ አድጓል ብለዋል። አሁን በ59 የትምህርት ክፍሎች በ82 የመጀመሪያ ዲግሪ፣ በ114 የ2ኛ ዲግሪ እና በ28 የሶስተኛ ዲግሪ ትምህርት ፕሮግራሞች አጠቃላይ ከ29ሺ በላይ ተማሪዎችን በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ መርሃ ግብሮች በማስተማር ላይ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

ዩኒቨርሲቲው የእለቱ ተመራቂዎችን ጨምሮ እስከ አሁን 72ሺ 624 ሙያተኞችን በማፍራት ለሀገሪቱ የሰው ሀብት ልማት አስተዋጽኦ ማበርከቱንም ጠቁመዋል።

በአዲሱ የሀገራችን የትምህርትና ስልጠና ፍኖተ ካርታ መሰረት ዩኒቨርሲቲው የምርምር ዩኒቨርሲቲ ሆኖ እንዲሰራ የተለየ መሆኑን ተከትሎ ለሀገሪቱ ልማት ተፈላጊ የሆኑ ፕሮግራሞችን ከፍቶ የማስተማርና የምርምር ተግባሩን አጠናክሮ መቀጠሉንም ተናግረዋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በ2014 በጀት አመት 747 (64 በመቶ) የሚሆኑ መምህራን በምርምር ስራ ታሳታፊ እንደነበሩ ጠቅሰው፣ 114 ሚሊዮን ብር ለምርምር ስራ መዋሉንም ገልጸዋል።

በመጨረሻም ተመራቂዎች ከዩኒቨርሲቲው ያካበቱትን እውቀት፣ ክህሎትና መልካም አስተሳሰብ በመጠቀም በተቋማት ውስጥ ተቀጥረውም ይሁን በግላቸው ስራ ፈጥረው አመርቂ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ጥሪ አቅርበዋል።

ሌላው በመርሃ ግብሩ ላይ በክብር እንግድነት ተገኝተው ንግግር ያደረጉት ክቡር አቶ ፈጠነ ተሾመ የብሄራዊ ሜትሮዎሎጂ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተርና የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ስራ አመራር ቦርድ አባል ሲሆኑ እውቀት የማይከስር ሀብትና የሁሉም ነገር መሰረት ሆኖ ማህበረሰብን የሚያሸጋግር እንደሆነ ገልጸዋል። ተመራቂዎች በትምህርት ቆይታቸው ወቅት በንድፈ ሃሳብና በተግባር ያገኙትን እውቀት በሚሰማሩበት የስራ ዘርፍ ሁሉ ለዘላቂ እድገትና ሽግግር እንዲጠቀሙበትም አሳስበዋል።

የኮቪድ 19 ወረርሽኝ፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ያሳደሩብንን ተጽእኖዎች እንዲሁም በሀገራችን ላይ የተቃጣውን ጦርነት በመመከት የጀመርናቸውን ሁሉን አቀፍ ልማት ለማከናወን እየተጋን ባለንበት ወቅት የተመረቃችሁ መሆናችሁ ልዩ ያደርጋችኋል ብለዋል። ችግር ፈቺ ሙያተኞች፣ ሕዝባችሁና ሀገራችሁ የሚጠብቁባችሁን አደራ የምትወጡ፣ በቅንነት የምታገለግሉ፣ ለሀገራችሁ እንቆቅልሽ የመፍትሄ አካል በመሆን በምትሰለፉበት የስራ መስክ ሁሉ የበኩላችሁን የምትወጡ እንድትሆኑ አሳስባለሁ ብለዋል።

በመርሃ ግብሩ ላይ የጋሞ ዞና አስተዳዳሪ አቶ ብርሃኑ ዘውዴ፣ ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴርና ከሌሎች የፌዴራልና የክልል መስሪያ ቤቶች የተጋበዙ እንግዶች ፣ የሃይማኖት አባቶች ፣ ግጭትን በእርጥብ ሳር የማብረድ እሴትን ያኖሩት የጋሞ ሽማግሌዎችና የተመራቂ ቤተሰቦች ተገኝተዋል። የአርባ ምንጭ ከተማ የኪነት ቡድን የተለያዩ ባህላዊና ዘመናዊ ዘፈኖችን በመጫወት የአዳራሹን የደስታ ድባብ አድምቀዋል።

በእለቱ በተከናወነው የምረቃ መርሃ ግብር በመጀመሪያ ዲግሪ 2062፣ በ2ኛ ዲግሪ 490 እና በ3ኛ ዲግሪ 9 በድምሩ 2ሺ 561 ተማሪዎች መመረቃቸው ታውቋል።



አቶ አማኑኤል ተሾመ

# ከተሞች መሪ ፕላኖቻቸውን በአግባቡ ተግባራዊ አለማድረጋቸው ለእድገታቸው እንቅፋት መሆኑ ተገለጸ

**ፀጋዬ ጥላሁን**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ከተሞች መሪ ፕላኖቻቸውን በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ባለመቻላቸው ለእድገታቸው እንቅፋት እንደሆነባቸው የኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማህበር ገለጸ፡፡ የዓለም አቀፍ ከተማ ደረጃ ለመድረስ እንዲሁም ለነዋሪዎቹ ምቹ ለመሆን ብዙ መስራት እንደሚጠበቅባቸውም ተጠቁሟል፡፡

የኢትዮጵያ አርክቴክቶች ማህበር ፕሬዚዳንት አማኑኤል ተሾመ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ከተሞች መዋቅራዊ ፕላኖቻቸው መሬት ባለመንካታቸው መዋቅራዊ ፕላኑ የሚለውና እነሱ የሚያድጉበት አቅጣጫ ፍፁም የተለያየ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ አዲስ አባባ ከተማን ጨምሮ የኢትዮጵያ ከተሞች የዓለም አቀፍ ከተማ ደረጃ ለመድረስ ብዙ ርቀት ላይ ናቸው፡፡

ከተሞቻችን መዋቅራዊ ፕላን ቢወጣላቸውም፤ በፕላኑ መሰረት እያደጉ አይደለም፡፡ በሁሉም ደረጃ ያሉ ከተሞች መዋቅራዊ ፕላን ያለመተግበር ችግር አለባቸው ብለዋል፡፡

ለአብነትም አዲስ አበባ ዓለም አቀፍ ከተማ ደረጃ ለመድረስና ለነዋሪዎቿ ምቹ ከተማ ለማድረግ ብዙ ስራዎች ይቀሯታል፡፡ የከተሞች መሪ ፕላን (እቅድ) መሬት ሊነካ ባለመቻሉ ለከተሞች እድገት እንቅፋት ሆኗል፡፡ ይህን ለመቀየር የኢትዮጵያ ከተሞች አዲስ አበባን ጨምሮ ብዙ መስራት ይጠብቃቸዋል፡፡

ነገር ግን እንደከተማ ተዋቅሮ እቅድ ውስጥ ተካትቶ ባይሰራም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአዲስ አበባ ከተማን ገፅታ ለመቀየር የሚደረጉ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ሙከራዎችና ውጤቶች ለአገራችን ተስፋ ሰጪ ናቸው፡፡

በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በአዲስ አበባ ከተማ የተጀመሩ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተስፋ ሰጪ ቢሆኑም እንደነሱ አይነት ብዙ ፕሮጀክቶች ያስፈልጉናል፡፡ ከተማዋ ለነዋሪዎቿና ለጎብኚዎች ምቹ ከተማ እንድትሆን ገና ብዙ የቤት ስራዎች ይጠብቋታል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

መንግሥት እንደአንድ ትልቅ አልሚ የከተሞችን እቅድ ሲወጣ ተከታትሎ በማስፈፀም፣ መስመር በማስያዝና በማስተግበር ዋና መሪነት ሚናውን ሊጫወት ይገባል። ስትራቴጂክ የሚባሉ ፕሮጀክቶችን መንግሥት ቀድሞ በመስራት ለሌሎች አልሚዎች አርአያ መሆን እንዳለበትም አሳስበዋል፡፡

መሰረተ ልማቶች ለከተሞች ምቹነት ቁልፍ ሚና ስላላቸው እነሱ ላይ ትኩረት በማድረግ እንደቅደም ተከተላቸው ቅርጽ መያዝ እንደለባቸው የገለፁት ፕሬዚዳንቱ፣ ለአብነትም እንደአብርሆት አይነት ቤተ መጻሕፍት በአዲስ አበባ በየአካባቢው ያስፈልጋል ብለዋል።

የከተሞችን እድገት ቅርጽ ለማስያዝና በእቅድ እንዲመራ ለማድረግ የሰው ሃይል ላይ ትልቅ ኢንቨስትመንት ያስፈልጋል ነው ያሉት አቶ አማኑኤል፤ ከተማ ላይ የሚፈፀመው የጥፋት ውጤት ወዲያውኑ የሚታይ ባለመሆኑ በሙያቸው ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ባለሙያዎችና አመራሮች በጥንቃቄ መመደብ እንደሚያስፈልግ አብራርተዋል፡፡

በተለይ በፕላንና ልማትና መሰል መስሪያ ቤቶች የሚሰሩ ባለሙያዎችና አመራሮች ለከተሞች እድገት በጣም ወሳኝ ባለሙያዎች በመሆናቸው በእነሱ ብቃት ላይ የተለየ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡

እንደ አቶ አማኑኤል ገለጻ፤ ውጤቱ የሚታየው በባለሙያዎቹ ብቃት ልክ ነው፡፡ ጥሩ ባለሙያዎች ካሉ ጥሩ ውጤት ስለሚኖረው ከተሞች በተለይም አዲስአበባ ጥሩ ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች መመራት የተሻለ ነው፡፡

# የጅግጅጋ መብራት ኃይል ማስፋፊያ ፕሮጀክት ተመረቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ:- የሱማሌ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ መሀመድ የጅግጅጋ ከተማ የኤሌክትሪክ ኃይል ማከፋፈያ ማስፋፊያ ፕሮጀክትን በይፋ መረቁ፡፡

ከተማዋ ቀደም ሲል 17 ዓመታት ከነበራት 12 ሜጋ ቮልት ላይ 31 ሜጋ ቮልት በመጨመር በአሁኑ ወቅት በአጠቃላይ 43 ሜጋ ቮልት እንድታገኝ መደረጉን የክልሉ ኮሙኒኬሽን መረጃ ያመላክታል፡፡

አቶ ሙስጠፌ በመርሐ ግብሩ ላይ ባደረጉት ንግግር፤ የሱማሌ ክልላዊ መንግሥት ከለውጡ በኋላ የኤሌክትሪክ ኃይልን ጨምሮ ለሕብረተሰቡ ኑሮ ወሳኝና መሰረታዊ የሆኑ አገልግሎቶችን ማሻሻል ላይ በትኩረት እየሠራ ነው ብለዋል፡፡



የክልሉ መንግሥት ላለፉት አራት ዓመታት የሕዝብ ማሕበራዊ ልማት የጀርባ አጥንት የሆኑትን የመብራት፣ የውሃና የመንገድ መሰረተ ልማቶች በልዩ ትኩረት መሥራቱንም ገልጸዋል፡፡

# ኢትዮጵያን ለነገው ትውልድ ስናስረክብ ምቹ የመኖሪያ አካባቢን ጭምር መሆን አለበት

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ:- "ኢትዮጵያን ለነገው ትውልድ ስናስረክብ ምቹ የመኖሪያ አካባቢን ጭምር መሆን እንዳለበት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትሩ ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ አሳሰቡ። ሚኒስትሩ በቦሌ ክፍለ ከተማ የ10 አቅመ ደካሞች ቤቶች እድሳት መርሀ ግብርም አስጀምረዋል።

የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከፍተኛና መካከለኛ አመራሮች የ4ኛ ዙር የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብርን በፒኮክ መናፈሻ ከ1000 በላይ ችግኞች በመትከል አስጀምረዋል፡፡

ከሶስት ዓመት በፊት ስለአረንጓዴ አሻራ ዘመቻ ሲወራ ጊዜያዊ ይመስል ያሉት ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ ዛሬ ላይ ከህጻናት እስከ አዛውንቱ ስለ ችግኝ መትከል እና በባለቤትነት የመንከባከብ ግንዛቤ ተፈጥሯል ብለዋል። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያውያን አዛውንቶች እና የሃይማኖት አባቶች በአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሩ እየተሳተፉ መሆናቸውንም አመላክተዋል።





የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴርም የዚህ አካል መሆኑን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ ውሃ ሕይወት እንደሚሰጥ ሁሉ ለራሱም ሕይወት ይፈልጋል፤ ውሃ ሕይወት እንዲኖረው ከፈለግን ለሰው ብቻ ሳይሆን ለውሃም ምቹ አካባቢ መፍጠር ይገባል ብለዋል፡፡

አካባቢን ማልማት ችግኞችን መትከል፣ ተፋሰሶችን መጠበቅ፣ ምንጮች እንዲጎለብቱ ማድረግ የውሃ ሀብት ለማልማት አስፈላጊ እንደሆኑም ጠቁመዋል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የ10 አቅመደካሞችን ቤት የማደስ እና በቀን አንድ ጊዜ መብላት ለማይችሉ 20 አቅመ ደካማ እማወራዎች የማዕድ ማጋራት ሥራም አከናውኗል፡፡

የቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ አራት ዋና ስራ አስፈጻሚ ወይዘሮ ትዕግስት ለገሰ በበኩላቸው እንደገለጹት የአቅመ ደካማ ቤቶችን በማደስ ስራ ከሌሎች ባለሀብቶች እና በጎ ስራ ከሚሰሩ የሃይማኖት ተቋማት ጋር በመሆን በወረዳው 50 ቤቶችን ለማደስ ታቅዶ 30 ቤቶችን የማደስ ስራ ተጀምሯል ብለዋል። ከእቅድ በላይ ለመስራት ፍላጎት እንዳለም ጠቁመዋል።

"ምግቤ ከበሬ" በሚለው መርሀ ግብርም የኑሮ ውድነት ጫናውን ለመቋቋም እና የገቢ ምንጭ ለመጨመር የሚያስችል እና አነስተኛ ኑሮ ላይ የሚገኙ የወረዳው ነዋሪዎችን የማገዝ ስራ እየተሰራ መሆኑንም ገልጸዋል።

በወረዳው በአራተኛው ዙር ከ20 ሺህ በላይ ለመትከል የታቀደው ተግባራዊ ሆኗል ያሉት ከ500 በላይ አቅመ ደካማ እና በዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ የሚገኙ እናቶች ፣ ወላጅ አልባ ሕጻናት፣ ኤች አይቪ ቫይረስ በደማቸው ለሚገኝ ህጻናት እና ለአካል ጉዳተኞች ማዕድ የማጋራት ስራ በተከታታይ የሚደረግ መሆኑንም አመላክተዋል።

# ኢንዱስትሪዎች የሚለቁትን በካይ ጋዝ ለመከላከል ችግኞችን መትከል ግድ እንደሚል ተገለጸ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስአበባ:- ኢንዱስትሪዎች የሚለቁትን በካይ ጋዝ ለመከላከል ችግኞችን በብዛትና በዓይነት መትከል ግድ እንደሚል የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል እንደተናገሩት በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚካሄደውን የችግኝ ተከላ መርሃግብር ባለፈው ቅዳሜ ባስጀመሩበት ወቅት እንደተናገሩት፤ ኢንዱስትሪዎች አካባቢን በመበከል ረገድ በቀዳሚነት የሚሰለፉ በመሆናው በሚገነቡባቸው አካባቢዎች በታቻለ መጠን የሚያመነጪቸውን የካርቦንዳይ አክሳይድ በካይ ጋዞች ለመቀነስ ችግኞችን መትከል ይገባል፡፡

በኢንዱስትሪ ፓርኮች የችግኝ ተከላ ስራን በመጀመራችን ብዙ ትርጉም አለው ያሉት አቶ መላኩ፤ ይህም ከኢንዱስትሪዎች ልማት ጋር አብረን አረንጓዴ ኢኮኖሚን እንድንገነባ ያስችለናል ብለዋል፡፡

በተለያዩ ጊዜያት የተሰሩ ስራዎችም ጥሩ ውጤት ላይ ያሉ መሆናቸውን በመጠቆም የበለጠ አጠናክሮ መሄድ መቻል አለብን ሲሉ አቶ መላኩ ተናግረዋል፡፡

ኢንዱስትሪዎች አካባቢያቸው ለሰራተኞቻቸው ሳቢና ማራኪ፣ ለስራ ምቹ እንዲሆኑና የሚያመነጩትን በካይ ጋዝ ወደራሳቸው ሊመጡ የሚችሉ ዛፎችን እየተከሉ እንዲሄዱ ማድረግ ባህል እንዲሆን የማስተማር ሥራ መስራት እንደሚገባም ጠቁመዋል፡፡

አገራችንና ዓለማችን ትልቁ ችግር እየሆነ ያለው የተፈጥሮ ሀብት መራቆት ነው ያሉት ሚኒስትሩ፣ ያንን ተከትሎ የሚመጣው የአየር ንብረት መዛባት፣ ድህነት፣ የፖለቲካ ቀውስ፣ አብዛኞቹ ነገሮች ከድህነትና አየር ንብረት መዛባት ጋር ተያይዘው የመጡ ናቸው ብለዋል፡፡

እንደ አገር የጀመርናቸው የልማት ስራዎች ሊሳኩ የሚችሉት የዜጎችና አገልግሎት ዘርፉ ላይ ያሉት ሰራተኞች ቀናነትና ትብብር ሲኖር ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ አገርን ለመለወጥ፣ ለማልማት፣ ለማሳደግ፣ ሳንታክት ከሰራን አሁን ካለንበት የኑሮ ውድነት፣ የፀጥታ ችግር፣ የውስጥና የአጎራባች አገራት ትንኮሳና ችግሮችን መቀለበስ እንችላለን ብለዋል፡፡

በአገራችን እየተስተዋሉ ያሉት ግጭቶች ምንጭ የኢኮኖሚው አለማደግ ነው፡፡ ሀገርን ለማሻሻል ኢንዱስትሪዎቻችን መሻሻል አለባቸው፣ ይህ ደግሞ የሁሉም ኃላፊነት ነው፣ ለአገራችን ሁሉንም ዋጋ ከፍለን ኃላፊነታችንን መወጣት አለብን ሲሉ አቶ መላኩ በአጽኖት ተናግረዋል፡፡

በ2013ዓ.ም በመስሪያ ቤቱና ተጠሪ ተቋማት አመራሮችና ሰራተኞች በአረንጓዴ አሻራ ከተተከለው ችግኝ ውስጥ 82 በመቶ በላይ የሚሆነው መጽደቁን ገልጸው፣ የትላንቱንና መሰል የአረንጓዴ አሻራ የማሳረፍ መርሀ-ግበር በሌሎችም የኢንዱትሪ ፓርኮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ አሳስበዋል፡፡

# “ከወዳጅነት ጠላትነትን፣ ከልማት ጥፋትን ማጉላት የግል አመለካከት እንጂ የሚዲያ ተግባር አይደለም”

**-አቶ መሐመድ አህመድ**
**በኦሮሚያ ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት የባህልና ሚዲያ ጉዳዮች አማካሪ**

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በሕዝቦች መካከል ከወዳጅነት ጠላትነትን መስበክ፣ ከልማት ጥፋት ላይ ማተኮር የሚዲያ ተግባር ሳይሆን የግል አመለካከት በመሆኑ መጠንቀቅ እንደሚያስፈልግ በኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት የባህልና ሚዲያ ጉዳዮች አማካሪ አቶ መሐመድ አህመድ አመለከቱ፡፡

አቶ መሐመድ አህመድ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፣ የተለያየ ባህልና ታሪካዊ ዳራ ያላቸው ከ80 በላይ ብሔር ብሔረሰቦች በሰላም አብረው ለሚኖሩባት ኢትዮጵያ የሚያስፈልገው ከጥላቻ ይልቅ ፍቅር፣ ከልዩነት ይልቅ አንድነት፣ ከጥፋት ይልቅ ልማትን የሚያጎላ የሰላም ሚዲያ ነው፡፡ ለከፋ ችግር ተጋልጠው የነበሩ እንደነሩዋንዳ እንዲሁም ከብተና አፋፍ ላይ ያሉ እንደነ ኢራቅ፣ የመንና ሶሪያ ያሉ የዓለም አገሮች ጀርባ የሚዲያ ሚና ከፍተኛ ነበር ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦች አገር መሆኗ አንድ ነገር ሆኖ በውስጥና በውጭ ሃይሎች ጫና ተወጥራ ባለችበት በአሁኑ ጊዜ ሚዲያዎች አፍራሽነት ከታከለበት ፈተናው ቀላል እንደማይሆን ያሳሰቡት አቶ መሐመድ፣ ከዚህ አንጻር ሕዝቡ ትንፋሹን በመሰብሰብ በዙሪያችን ያንዣበቡ ጠላቶችን በአንድነት እንዲመክት ለአገሪቱ የሚያስፈገው ሚዲያ ሚዛናዊ የሆነ የሰላም ጆርናሊዝም መርሆን የተከተለ መሆን እንዳለበት አስገንዝበዋል፡፡

በሩዋንዳ እንደቀላሉ ተጀምሮ ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ ወደ ሚሊዮን የሚጠጋ ሕይወት የቀጠፈው ዘግናኝ የዘር ፍጅት በውሸት መረጃ ያቀጣጠሉና ሕይወታቸውን ለማትረፍ የሸሹ ሰዎች እንዳያመልጡ የት እንዳሉ አቅጣጫን በማሳየት ገዳዮቹን የመሩ በተለይ በወቅቱ የኤፍ.ኤም ሬዲዮኖች እንደነበሩ በታሪክ የተመዘገበ ጉዳይ መሆኑን የጠቀሱት አቶ መሐመድ፣ በእርስ በእርስ ጦርነት እየታመሱ ያሉና የመበተን አፋፍ ላይ የሚገኙ እንደ ኢራቅ፣ ሊቢያ፣ የመንና ሶሪያ ያሉ አገራት በውጭ ፈንድ የሚደረጉ ሚዲያዎች ጭምር ጦርነቱ እየተፋፋመ መሆኑን መገንዘብ ጠቃሚ ነው ብለዋል፡፡

ዳሩ ግን በአገራችንም አገረ መንግሥቱን በሃይል ለመናድ ብሎም አገራዊ ለውጡን ለመቀልበስ የሞት ሽረት ትግል እያደረጉ ያሉ ሃይሎች በዋናነት የሚዲያ ጉልበት በመጠቀም መሆኑን የገለጹት አማካሪው፣ አንዳንድ የአገራችን ሚዲያዎች በስማቸው መደበኛ ይሁኑ እንጂ በሥራቸው ከሚዲያ መርሆ ባፈገጠ መልኩ ሁለት ቦታ በመቆም ጠላትንም ወዳጅንም እኩል ሲያገለግሉ ማየት እየተለመደ መምጣቱን አመልክተዋል፡፡

ከሁሉም በላይ በሕጋዊ መንገድ ተቋቁመው ሕገወጥ ተግባር የሚፈጽሙ ሚዲያዎች ካልተፈተሹ እስካሁን ካስከተሉት ጥፋት የከፋ ጥፋት ለመፈጸም ወደ ኋላ እንደማይሉ ያሳሰቡት አማካሪው፣ በማህበራዊ ሚዲያ ረገድም በሃላፊነት የሚሰሩ ወገኖች እንዳሉ ሁሉ ጭር ሲል የማይወዱ አካላት የጎማ ፍንዳታ የቦምብ ፍንዳታ፣ የሁለት ሰዎች ጠብ ብሔር ወይም አገራዊ መልክ በማስያዝ አገር እንዳይረጋጋ እየሰሩ መሆናቸውንም አስታውቀዋል፡፡

እንደ አማካሪው ማብራሪያ፣ ሚዲያ እውነትን፣ ፍትሃዊነትን፣ እኩልነትንና ወንድማማችነትን ይሰብካል፡፡ ማንም ሰው እውነትን በመወገን ሃሳቡን በነጻነት የመግለጽ መብት አለው፡፡ ሆኖም ግን ነባራዊ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አንዱ የሚዲያ መርሆ ነው፡፡ በፈረሰች አገር ውስጥ ይቅር ነጻነት በሕይወት ለመኖር ራሱ ከባድ መሆኑን ማመዛዘን ያስፈልጋል፡፡ ለሚዲያ የመረጃ ምንጭ የሚሆኑ ሰዎች በተለይ በአሁኑ ጊዜ ጤናማ አስተሳሰብ ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ የግድ ይላል፡፡

# አብርኆት ቤተ መጻህፍትን ለማቋቋም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሚያምን ትውልድ ለማፍራት የሚያስችል መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ለኢትዮጵያውያን እንዲያገለግል ታስቦ የተሰራና ከኬኔዲ ቤተ መጻህፍት ቀጥሎ ለቤተ መ መጻህፍትነት ታስቦ የተገነባ መሆኑንና በቤተ መጽሀፉ ሊኖሩ የሚገባቸውን መጻህፍቶችን ማሰባሰብ መቻሉንም ተናግረዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ በቤተ መጽሀፉ በየቀኑ ከ10ሺ ሰዎች በላይ እንደሚስተናገዱ፣ የእውቀት መገብያ፣ የቱሪስት መዳረሻ ቦታ መሆኑን፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እያስተዳደረው መሆኑንና ቤተ መጻህፍቱ የተሰራበት የጥበብና የአገልግሎት ደረጃ ተጣምረው የተሻለ አገልግሎት የሚሰጥበት ቦታ እንደሚያደርጉትም ተናግረዋል፡፡

ሕጻናት፣ አረጋውያን፣ እናቶች ጭምር እንደእንጨትና እንስራ ውሃ ተሸከመው የለገሱበት፣ የማሕበረሰብ የመገናኛና መተዋወቂያ ቦታ መሆኑን የተናገሩት ዲያቆን ዳንኤል፤ በርካታ የአብርኆት ቤተ መጻህፍት በየክልሉ፣ በየዞኑ በየወረዳው እስኪኖሩ ጥረቱ እንደሚቀጥልም ገልጸዋል፡፡

እንደ ሙአዘጥበባት ዲያቆን ዳኤል ገለጻ፤ እውቀትና ንባብ ላይ መስራት አገር የሚገነባ ትውልድ ለማፍራት የጎላ ሚና አለው፣ በመሆኑም በአገር አቀፍ ደረጃ በየአካባቢው እንደ አብርሆት አይነት ቤተ መጻህፍት እስኪቋቋም ድረስ ጥረቱ እንደሚቀጥልም ሙአዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ተናግረዋል።

ከውጭ የሚገቡ ኢትዮጵያውያን ወደ አገራቸው ሲገቡ ለአብርኆት በመጽሃፍ ልገሳ የሚያደርጉትን ጥረት እንዲቀጥሉም ነው የጠቆሙት፡፡ ‹‹ኢትዮጵያን ጠየቃችሁ የምንለው አብርኆት መጥታችሁ መጽሃፍ ስታበረክቱ ነው›› ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ፕሮፌሰር ጣሰው ወልደሃና በበኩላቸው፤ መጻህፍት ተሰብስቦ የሚያልቅ አይደለም፣ መጽሃፍ ማንበብ የሕይወት ዘመን ስራ እንደመሆኑ የማሰባሰብ ተግባሩ ቀጣይ ሊሆን ይገባል ብለዋል።

ቤተ መጽሃፍቱ ኢትዮጵያውያን የማንበብ ባህላቸውን እንዲያዳብሩ በእውቀት በመመራት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ኑራቸውን እንዲያሻሽሉና አገርን እንዲመሩ ለማስቻል ከፍተኛ ሚና እንደሚያበረክትም ነው ፕሮፌሰር ጣሰው የተናገሩት።



የአብርኆት ቤተ መጻህፍትን መጻህፍት ለመሙላት በተደረገው ርብርብና ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በተሰጠው መጻህፍት ለማሰባሰብ ‹‹ሚሊዮን መጻህፍት ለሚሊኒየሙ ትውልድ›› በሚለው መርሃ ግብር ኮሚቴ ተዋቅሮ መርሃ ግብሩ ሲካሂድ መቆየቱም ተገልጿል፡፡

በሂደቱ 455 ሺህ 403 መጻህፍት የተሰበሰበ መሆኑን፤ ከ 77 የመንግሥትና የግል ድርጅቶች 368 ሺህ 794 መጻህፍት እንዲሁም ከአንድ ሺህ 199 ለጋሽ ግለሰቦች 86 ሺህ 609 መጻህፍት መሰብሰቡም በእለቱ በቀረበው ሪፖርት ተገልጿል፡፡

መጻህፍቶቹ ህጻናት በቀላሉ ሊረዷቸው የሚችሉና በተለያዩ የትምህርት አይነት የተዘጋጁ ወቅታዊ፣ ጠቃሚና አስፈላጊ እንደሆኑም ነው የተገለጸው፡፡

በተለይ የጉምሩክ ኮሚሽን፣ ኦሮሚያ ክልል መስተዳድር፣ የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል፣ ገንዘብ ሚኒስቴር በማሰባሰብ ተግባሩ ከፍተኛ አስተዋጽ በማበርከት ተመስግነዋል፡፡

መጽሃፍትን በማሰባሰብና በማስተባበር ብዙሃን መገናኛ እንዲሁም ግለሰቦችና የእድር ማህበራት ላበረከቱት አስተዋጽኦም ምስጋናና እውቅና ተሰጥቷቸዋል፡፡

መርሃ ግብሩ የተመራው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የአዲስ አበባ ባህል ቱሪዝም ቢሮ፣ የአዲስ አበባ ኮሙኒኬሽን፣ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበርና የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት በጋራ በተዋቀረ ኮሚቴ መሆኑም ተጠቁሟል፡፡

በእለቱ በማሰባሰቢያ መርሃ ግብሩ ተሳትፎ እውቅና ከተሰጣቸው መካከል ልጃቸው የተማረችበትን መጽሀፍት በጀርባቸው አዝለው በቤተ መጻህፍት በመገኘት ያበረከቱት ወይዘሮ በላይነሽ ተክለስላሴ፤ ውጤት ያለው የተማረ ሰው በመሆኑ ትውልዱ እንዲማርበት በማሰብ ልጃቸው የተማረችበትን መጽሃፍት ማስረከባቸውን ተናግረዋል፡፡ በእውቅናው እንደተደሰቱና ሌሎችም የእርሳቸውን ፈለግ ሊከተሉ እንደሚገባም ተናግረዋል፡፡

በጫማ መጥረግ ስራ የሚተዳደረውና በልገሳው የተሳተፈው ወጣት ታሪኩ ወዬሳ በበኩሉ እንደተናገረው፤ ‹‹ለእኔ መጻህፍት የሕይወት አጋሬ፣ ጓደኛዬም ነው፡ ፡ ለመለገስ የወሰንኩት ከመጻህፍት ያገኘሁትን ጥቅም ሌሎችም እንዲያገኙ በማሰብ ነው፡፡ መጻህፍት አእምሮን የሚገነባ በመሆኑ ትውልዱ ሊያነብ ይገባል››፡፡

ጥሩ ነገር ማድረግ ያስደስታል፣ በሕይወት እስካለሁ እያነበብኩ እቀጥላለሁ፤ ይህ ደስታዬ ነው፡፡ እውቅናው ለበለጠ ስራ ብርታት እንደሰጠው እና ባደረገው ልገሳም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ጭምር በስልክ ማመስገናቸውን ጠቅሶ፤ እኔም በተራዬ ላመሰግናቸው እፈልጋለሁ ብሏል፡፡

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም ለአብርኆት ቤተመጻህፍት በሶስት ዙር መጽሀፍ አሰባስቦ ያስረከበ ሲሆን፤ በመጀመሪያው ዙር አምስት ሺህ መጻህፍት በአምስት ቀን በሚል 5000 መጻሕፍትን፤ በእድሜ ልክ አንጋፋ ደራስያን ስም ባካሄደው መርሀ ግብሩ 10,400 መጻህፍትን እንዲሁም ስለኢትዮጵያ በሚለው መርሀ ግብሩ 1273 መጻህፍት በጥቅሉ በሶስት ዙር 16 ሺህ 673 መጻህፍትን በማበርከቱ እውቅናና ምስጋና ተሰጥቶታል፡፡

# ሕወሓት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሕወሓት መስራችና ፖለቲከኛ የሆኑት ኢንጅነር ግደይ ዘርአፅዮን በተለይ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለሚታተመው ወጋሕታ ጋዜጣ እንደተናገሩት ለሰላም የሚያቀራርብ ሃሳብ እንጂ ከወዲሁ ቀይ መስመር በማስመር ሰላምን ማምጣት አይቻልም፡፡

እንደ ኢንጂነር ግደይ ገለፃ፣ የሕወሓት ቡድን ለሰላም ዝግጁ ነኝ እያለ ቀይ መስመር ናቸው ብሎ ያስቀመጣቸው ነጥቦች ለውይይት የሚያቀራርቡ ሳይሆን ከወዲሁ ውይይት እንዳይካሄድ የሚያራርቁ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ የሚያሳየው ቡድኑ ለሰላም ዝግጁ አለመሆኑን ነው፡፡

እንዲህ አይነት አካሄድ ለሕወሓትም ሆነ ለትግራይ ሕዝብ የሚጠቅም አይደለም ያሉት ኢንጂነር ግደይ፤ ለችግሮች ሁሉ መፍትሄው ውይይት እንጂ ጦርነት አይደለም ብለዋል።

ችግሩ እንዲፈታ ከተፈለገ የሰላም ንግግሮች አስፈላጊ ናቸው፤ መንግሥትም ለዚህ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው። ነገር ግን ሕወሓት ከወዲሁ ያነሳቸው ነጥቦች ለሰላም እንቅፋት በመሆናቸው ለትግራይ ሕዝብም ሆነ ለሕወሓት የማይጠቅሙ ናቸው ብለዋል።

ጦርነቱ እንዲቆም ከተፈለገ ሰላምና የሚያቀራርቡ ሃሳቦችን ይዞ መቅረብ ያስፈልጋል ያሉት ኢንጂነር ግደይ፤ ቀይ መስመር እያስቀመጥክ እደራደራለሁ ማለት የሚያስኬድ አይደለም፤ ይህ በሰላም ለመፍታት ፍላጎት አለመኖሩ የሚያማላክት ነው ብለዋል፡፡

ሕወሓት ሕዝብ ከሕዝብ የሚያቀራርብ ሃሳብ ይዞ መቅረብ አለበት፤ የትግራይ ሕዝብ ፍላጎት በሰላም ከሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ጋር አብሮ መኖር ነው፤ ጦርነት ለትግራይ ሕዝብም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አይጠቅምም ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ኢንጂነር ግደይ ገለጻ፣ ሕወሓት ከፖለቲካዊ እልህ ወጥቶ የትግራይን ሕዝብ የሚጠቅም መንገድ ሊከተል ይገባል፤ ሕዝብ ከሕዝብ ጋር በሰላም አብረው እንዲኖሩ ሃሳብ ማቅረብ ያስፈልጋል፤ የትግራይ ሕዝብ ከዚህ በፊት ብዙ ጦርነቶችን አሳልፏል፤ ነገር ግን ተጎድቷል እንጂ የተጠቀመው ነገር የለም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ በችግር ይሁን በሰላም ለዘመናት ተደጋግፎ የመጣ ሕዝብ ነው፤ ተነጣጥሎ የሚኖር አይደለም፤ በተለይ ጎረቤት የሆነ የአማራ ሕዝብ ወዳጅ እንጂ አንዳንድ ፖለቲከኞች እንደሚሉት ጠላት አይደለም። በርካታ የትግራይ ተወላጆች ወደ አማራ ክልል ተፈናቅለው መጥተው በሰላም እየኖሩ ናቸው ብለዋል፡፡

በሕዝቦች መካከል ምንም ችግር የለም፤ ለትግራይ ሕዝብም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የማይጠቅሙ ሃሳቦችን ማንሳት ተገቢ አይደለም። በተለይ የትግራይ እና የአማራ ሕዝቦች በባህል፣ ቋንቋ እና ሃይማኖት የተሳሰሩ ናቸው፤ ለዘመናት አብሮ የኖረና ለወደፊትም አብሮ የሚኖር ሕዝብ ናቸው ብለዋል።

ከጦርነት መንፈስ መውጣት ነው የሚያስፈልገው ያሉት ኢንጂነር ግደይ፤ በዚህ ዘመን ጦርነት መፍትሄ አይደለም፤ በጦርነት ተያይዘህ ትጠፋለህ እንጂ ልታድግ አትችልም ሲሉ ተናግሯል።

ሕወሓት ሕዝብ ከሕዝብ የማያቀራርቡ ነጥቦችን በማስቀመጥ የትግራይን ሕዝብ ዳግም ወደ ጦርነት እንዳይከተው የትግራይ ሕዝብ ‹‹ሰላም እንጂ ጦርነት አንፈልግም፤ ከዚህ ቀደም በጦርነት መስዋእት ከመክፈል ውጪ ምንም የተጠቀምነው ነገር የለም›› በማለት ሕወሓት ላይ ተፅእኖ እንዲያሳድርም አሳስበዋል፡፡

# ፕሮጀክቱ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንዲህ ያለ ግዙፍ ፕሮጀክት በራስ አቅም በመገንባት ከተያዘለት ጊዜ ቀድሞ ማጠናቀቅ መቻል በታሪካችን የመጀመሪያ ነው፡፡ አገር በከፍተኛ ውጣ ውረድ ውስጥ እያለች ለችግሮች ባለመንበርከክ በራስ በጀት ይህን ትልቅ ፕሮጀክት አጠናቆ ለሕዝብ ማቅረብም ታሪካዊ ያደርገዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ስራ አስኪያጅ ኢንጅነር ዘሪሁን አባተ በበኩላቸው እንደገለጹት፣ ፕሮጀክቱ የሚታየውን የውሃ ችግር ለመፍታት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ነገር ግን አዲስአበባ በፍጥነት እያደገችና እየሰፋች በመሆኑ የሚስተዋለውን ችግር ሙሉ ለሙሉ መፍታት አይችልም ብለዋል፡፡

ለውሃው ፕሮጀክቱ 4 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ወጪ ተደርጎበታል ያሉት ስራ አስኪያጁ፤ የሆቴሎችና የልማት መበራከት፣ የሕዝብ ቁጥር መጨመርና የኢንዱስትሪዎች መብዛትን ተከትሎ የውሃ ችግርን በፍጥነት ለመፍታት እንቅፋት እየፈጠረ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሚስተዋለውን የውሃ ችግር ለመፍታት ስራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ገልጸዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያን ከነባር ችግሮቿ በማላቀቅ ወደ ብልጽግና ማሻገር

ኢትዮጵያ በረዥም ዘመናት የታሪክ ጉዞዋ ጥሩም ሆነ መጥፎ ታሪኮችን አሳልፋለች፡፡ጥንታዊና በአለም ታሪክ ጉዞ ውስጥ የጎላ ስፍራ ከሚይዙት ጥቂት ሀገራት አንዷ የሆነችው ሀገራችን የሰውል ልጅ መገኛ ፤የነጻነትና የአይበገሬነት ተምሳሌት ከመሆኗም ባሻገር የዘመናት ምኞት የሆነውን በአባይ ወንዝ ላይ በአፍሪካ ታላቁን የህዳሴ ግድብ በማልማት እና በቢሊዮኖች ችግኝ በመትከል ታሪክ እየሰራች ያለች ሀገር ነች፡፡

የሀገሪቱ ታሪክ በርግጥ እንደማንኛውም ሀገር ሁሉ በጎበጎውን ብቻ የያዘ አይደለም፡፡የጦርነት፤የርሃብ፤እርዛት ፤የመፈናቀልና የጥላቻ ትርክትን የያዙ ታሪኮችም ባለቤት ነው ፡፡ በተለይም የኢትዮጵያን አንድነትና ኋላቀርነትን የሚሹ የውጭ ኃይሎችና የውስጥ ባንዳዎች በየጊዜው በሚሸርቡት ሴራ ጸንቶ የቆየውን ሀገራዊ አንድትና መተሳሰብ በሰፊው እየተፈተነ ይገኛል ፡፡

ለነጻነታቸውና ለአንድነታቸው ቀናኢ የሆኑትን ኢትዮጵያውያን እርስ በእርስ በማጋጨትና በማባላት ሀገሪቱን እንደ ሀገር ለማፍረስ የሚተጉ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ከጥንት እስከዛሬ ሲፈታተኑን ኖረዋል ፤ዛሬም በተመሳሳ መልኩ ዕየተፈታተኑን ነው ፡፡

የቅኝ አገዛዝ ፍላጎቱን በኢትዮጵያ ላይ ለመጫን ቋምጦ የነበረውን የፋሺስት ኃይል አሳፍረው መመለሳቸው ያልተዋጠላቸው የውጭ ኃይሎች የኢትዮጵያ አንድነትና ጀግንነት ሲያባንናቸው ይኖራል፡፡በሃይል ለማንበርከክ ያልቻሉትን ህዝብም ያሉ ጥቃቅን ክፍተቶችን በማጉላትና ሰርስሮ በመግባት እርስ በእርሱ ለማጋጨትና ሀገሪቱን ለማፍረስ ያልተቆጠበ ጥረት ሲያደርጉ ኖረዋል፡፡

አልፎ ተርፎም ለሀገሪቱ መዳከምና በሂደትም መፈራርስ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚሉትን ሃይል በማደራጀት፤በማስታጠቅና በማሰልጠን ታሪካዊ ጠላትነታቸውን በገሃድ ሲያስመሰክሩ ኑረዋል፡፡ያለማፈርም ለፍፈዋል፡፡አሸባሪው ሕወሓትን የመሳሰሉ ወንበዴዎችን የልብ ልብ ሰጥተው፤አቅፈውና ደግፈው ለስልጣን በማብቃት ኢትዮጵያ በጊዜ ሂደት እንድትዳከምና ብሎም እንድትፈራርስ በረዥሙ አልመው ሰርተዋል፡፡

በዚህ ሂደት የመጣው የአሸባሪው ሕወሓት ኃይልም በገዛ ሀገሩ ላይ ጠላት ሆኖ ኖሯል፡፡ ከጌቶቹ የተሰጠውን ኢትዮጵያን የማፈራረስና ብሎም በኢትዮጵያ ፍርስራሽ ላይ የራሱን ኢምፓየር የመገንባት ህልም አንግቦ ለ27 አመታት ያህል ሀገሪቱን በጽልመት ውስጥ ሲገዛ ቆይቷል፡፡

ለኢትዮጵያ አንድነት ምሶሶ የሆኑ ብሄሮችን በማይጨበጥ ስሜት በማነሳሳትና የጥላቻ ትርክትን በማስፋፋት የሀገሪቱ ህልውና እንዲናጋ በብዙ ደክሟል፡፡ በየቦታው በሚሸርባቸው እኩይ ሴራዎችም ኢትዮጵያውያን በጥርጣሬ እንዲተያዩና በአንድነት እንዳይቆሙ የጥላቻ ሃውልት ሲያቆም ኖሯል፡፡

ሆኖም የኢትጵያዊነት መሰረቱ ጽኑ በመሆኑ ኢትዮጵያ ከመፈራረስ ይልቅ ለማፈራረስ ቀን ከሌሊት ሲሰራ የቆየውን ይህንን ኃይል በማሽቀንጠር ዳግም ሀገሪቱ በአዲስ የለውጥና የተስፋ ጎዳና መጓዝ ጀምራለች፡፡ ተዳክሞ የነበረው ኢትዮጵያዊነት ቀና ብሏል፡፡በሞት አፋፍ ላይ የነበረውን የህዳሴ ግድብ ነፍስ እንዲዘራ በማድረግ ጨልሞ የነበረው የኢትዮጵያውያን ተስፋ ለምልሟል ፡፡ጨለማን ገፎ ብርሃን መስጠት ጀምሯል፡፡

ከአፍሪካ አልፎ ለአለም ተምሳሌት የሆነ የአረምጓዴ አሻራ መርሃ ግብር እውን በማድረግ ኢትዮጵያን አረንጓዴ የማልበስ ስራ ከጫፍ እስከ ጫፍ በመከናወን ላይ ነው፡፡ በአለም ላይ ከነዳጅ ቀጥሎ ውድ የሆነውን የስንዴ ምርት በስፋት በማምረት ከራሷ አልፋ ወደ ጎረቤት ሀገራት ለመላክ በዝግጅት ላይ ነች፡፡

ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ የሀገሪቱ ለውጥ ያሳሰባቸው የቅኝ አገዛዝ መንፈስ የተጣባቸው ሀገሮችና በአባይ ውሃ ላይ ኢፍትሃዊ አካሄድን የመረጡ አካላት ዛሬም ኢትዮጵያን አኬል ዳማ ለማድረግ በመታተር ላይ ናቸው፡፡

አሸባሪዎቹን ሕወሓትና ሸኔን በተላላኪነት በማሰማራት ንጹሃን በግፍ እንዲያልቁ ፍርዳቸውን አሳልፈዋል፡፡ሁከትና ብጥብጥ እንዲነግስም የሰኔ ወርን እንደአምልኮ በመያዝ የጥፋት ድግሳቸውን በማጧጧፍ ሴቶች፤ህጻናትና አረጋውያን ላይ የግፍ በትራቸውን አሳርፈዋል፡፡

በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆነው በኢትዮጵያውያን ላይ ጦርነትና ሁከት ያወጁት ኃይሎች ለጊዜው የላኪዎቻቸውን ፍላጎት ያስፈጸሙ ቢመስላቸውም ለፈጸሙት ግፍ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚፋረድበት ቀን እሩቅ አይሆንም፡፡የጨለማው ጊዜ አልፎ ብርሃን መውጣቱ ፤የታሪካዊ ጠላቶቻችንና የባንዳዎቻቸውን ሴራ አክሽፈን በእድገትና በብልጽግና ጎዳና መጓዝ መጀመራችን ሩቅ አይሆንም፡፡ ከነባር ችግሮቻችን ተላቀን በአዲስ ተስፋ መንገድ ነገዎቻችንን ብሩህ የምናደርግበት የአስተሳሰብ መሰረት መገንባታችን አይቀርም ።


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# መከላከያ ትኩረቱ ሳይከፋፈል ለግዳጅ ዝግጁ እንዲሆን

**ቦጋለ አበበ**

ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ እንደ ጀግናው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ስራ የበዛበት በዓለም ስለመኖሩ አፍን ሞልቶ መናገር አይቻልም። ይህ ሰራዊት በዚህች ጥቂት ዓመት በብዙ ተግዳሮቶች ውስትጥ አልፏል፣ በከሃዲዎች ጀርባውን ተወግቷል፣ በራሱ ወገን ግፍ ተሰርቶበታል። ከመደበኛ ጦርነት ውጪም እዚህም እዚያም የሚከሰቱ የፀጥታ ችግሮች ለማስቆም ሌት ተቀን እየተጋ ነው ።

ይህ ሰራዊት በዋናነት የአገርን ዳር ድንበርን ከውጪ ወራሪ ሃይሎች በመጠበቅ ላይ ብቻ አልተወሰነም። በተለያዩ ክልሎች ሽብርተኛ ቡድኖች ንጹሃን ዜጎች ላይ የሚፈጽሙት የግፍ ግድያና ዘር ተኮር ጭፍጨፋ፣ግጭቶችና ሌሎችም ተመሳሳይ የጸጥታ ችግሮች ለሰራዊቱ ተጨማሪ ስራ ሆነውታል።

አገር እንዲህ በውጪም በውስጥም ጠላቶች እንደ ቆዳ ተወጥራ ባለችበት በዚህ ወቅት መከላከያ ሰራዊት በትንንሽ ግዳጆች ሲባክን ማየት አገርን ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል ብሎ ለመናገር ወታደራዊ ምሁር መሆንን አይጠይቅም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከገንዘብ፣ከቁሳቁስና ከሞራል ድጋፍ ባለፈ በምን መልኩ ሊደግፈው ይገባል የሚለው ጥያቄ የዚህ ጽሁፍ ዋንኛ ማጠንጠኛ ነው ። የዚህ ጥያቄ ምላሽ የሁሉንም ኢትዮጵያዊና የክልል መንግስታት ጥንካሬ እና ቀናኢነትን የሚሻ ይመስለኛል ፡፡ መከላከያ ሰራዊት እንዲህ በየቦታው በትንንሽ ግዳጆች እንዲወጠርና ስራ እንዲበዛበት ካደረጉ ምክኒያቶች በቅድሚያ ጥቂቱን መመልከት ሁሉም ኢትዮጵያዊ የመፍትሄው አካል እንዲሆን ሞራል ይሰጣልና በስሱ እንመልከተው።

የፈረደባት ይህች ሰኔ ወር የኢትዮጵያውያን የፈተናና የክፉ ወር መገለጫ እየሆነች መምጣቷ ለምን ነው? የሚለውን ጥያቄ መመለስ ከሁሉም ይቀድማል። በግልጽ እንደሚታወቀውና ባለፉት ጥቂት ዓመታት እንደተስተዋለው ሰኔ በመጣ ቁጥር ከታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ጋር በተያያዘ በየደረጃው የሚካሄደውን የውሃ ሙሌት ለማስተጓጎል የውጪ ሃይሎች የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። ለዚህም የውጪ ሃይሎች በቀጥታ ወረራ መፈጸም ባይችሉ እንኳን የአገር ውስጥ ባንዳዎችን ተጠቅመው ቢቻል አገር እንድትፈርስ ካልተቻለም እንዳትረጋጋ ለማድረግ ቁጭ ብለው እንደማያድሩ ለማንም ግልፅ ነው።

ሌላው ቢቀር ሰሞኑን የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ የወጡ በርካታ ዜጎች በራሳቸው አገር ወታደሮች እየተገደሉ ባለበት ሁኔታ የሰው ድንበር ገብቶ ‹‹በጣት የሚቆጠሩ ወታደሮቼ ተገድለዋልና ጦርነት ካልገጠምኩ›› የሚል ጩኸቱን ቀሙኝ አይነት ጫጫታ ለምን እንደተፈጠረ ነጠብጣቦችን መገጣጠም ኢትዮጵያ ላይ ስለሚዶለተው ሴራ ግልጽ ስእል ይሰጣል ።

ይህ እንዳለ ሆኖ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በአንድ ጊዜ የሚከሰቱ የጸጥታ ችግሮች በግልጽ መከላከያ ሰራዊትን አንድ ቦታ ላይ ትኩረት እንዳያደርግና በየቦታው በትንንሽ ችግሮች እንዲወጠር(decentralize) የማድረግ የውጪም የአገር ውስጥም ጠላቶች ስትራቴጂ መሆኑን በግልጽ ያሳያል።

ሰራዊቱን የውጪዎቹም ሃይሎች ይሁኑ የአገር ውስጥ ባንዳዎች ይፈሩታል። ገና ስሙ ሲጠራ የሚርዱ የጠላት ሃይሎች ይህ ሰራዊት ትኩረቱን አንድ ቦታ አድርጎ ተረጋግቶ ሊገጥሙት አይደለም ሊሞክሩት አይደፍሩም።ያላቸው ምርጫ ሰራዊቱ አንድ ቦታ ላይ ትኩረትና ሃይሉን እንዳይሰበስብ በማድረግ አቅሙን ማሳሳት ነው። ከዚያም እድላቸውን መሞከር ነው።

ይህ ስትራቴጂ ሰራዊቱን በብሔር መከፋፈል የተሰኘ ሌላም ገጽ አለው። ይህ አልተሳካም፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያዊ ሆኖ አሳፍሯቸዋል። ለዚህ ደግሞ አንድ ግልጽና ግልጽ ማሳያ ማቅረብ ይቻላል። በየአካባቢው በሚነሱ የጸጥታ ችግሮች ለመከላከል በወሰዳቸው ግዳጆች ይህንን በተጨባጭ አስመስክሯል፤ መካድ አይቻልም።

እርግጥ ነው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት እንዲህ ስራ ቢበዛበትም አገር ላይ የተጋረጠውን አደጋ ለመመከትና ለማስቀረት አቅሙም ዝግጅቱም አለው። የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትርና የጦር ሃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ዶክተር ዐቢይ አህመድ ደጋግመው ስለመከላከያ ሰራዊቱ የሚናገሩትም ይህንኑ ነው። ሰራዊቱ የሚዘጋጀው አገር ውስጥ እዚህም እዚያም ተበታትነው በንጹሃን ዜጎች ላይ የሽብር ተግባር ለሚፈጽሙ ቡድኖች አይደለም።

የሰራዊቱ ዝግጅትና አቅም ከዚህም ይልቃል። ሰራዊቱ ይህን ታላቅ አቅም ስላለው ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ በትንንሽ ግዳጆች እንዲወጠር መፍቀድ የለበትም። መንግስትም ቢሆን ይህን ጉዳይ ሳያስበው አይቀርም። ጉዳዩ አሳሳቢ ባይሆን እንኳን መከላከያ ሰራዊት በአንድ ቦታ ላይ ትኩረቱን ሰብስቦ ዝግጁ ሆኖ መቆየቱ የአገር ጠላቶች የሚፈልጉትን ጥቃት መፈጸም አይደለም እንዳያስቡት ሊያደርግ ይችላልና ሃሳቡ አይናቅም።

በዋናነት ሁሉም ኢትዮጵያዊ አካባቢውን በንቃት እየጠበቀ ከአካባቢው የጸጥታ አካላት ጋር በቅርበትና በመናበብ መስራት ይጠበቅበታል ። በየትኛውም እርከን ላይ ያሉ የጸጥታ አካላትም በተመሳሳይ ከሕዝብና በየክልሎቹ ከሚገኙ የተሻለ ዝግጅት እንዲሁም አቅም ካላቸው የጸጥታ አካላት ጋር ተናበው በመስራትና ለሚፈጠሩ ችግሮች አፋጣኝ ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል።

በየደረጃው የሚገኙ የደህንነት አገልግሎቶች አቅም ተጠናክሮና ዘምኖ ችግሮች ከመፈጠራቸው በፊት ማነፍነፍ እንዲችሉ ማድረግ ከተቻለ በውስጥ ጠላቶች የሚፈጠሩ ችግሮች ከአካባቢ ታጣቂዎችና ከክልል ልዩ ሃይሎች አቅም የበለጡ ሊሆኑ አይችሉም ። የሚፈጠሩ ችግሮች የቱንም ያህል ከአቅም በላይ ቢሆኑ እንኳን እንደሰሞኑ ምንም አይነት ጦር መሳሪያ ባልታጠቁና ራሳቸውን መከላከል በማይችሉ ንጹሃን ዜጎች ላይ የሚፈጠሩ ዘግናኝና አሳፋሪ ጭፍጨፋዎች የመደገም እድላቸው ጠባብ ይሆናል።

ይህን ተፈጻሚ ማድረግ ከተቻለ መከላከያ ሰራዊቱን በትንንሽ ግዳጆች ከመባከን ተረፈ ማለት ነው። በዚህም ትኩረቱን በሌሎች ዋና ዋና ችግሮች ላይ ማድረግ ይቻለዋል። ይህም ኢትዮጵያ በውስጥ ለሚገጥሟት ፈተናዎች ረጅም እጃቸውን የሚያስገቡ የውጪ ሃይሎች ቆመው እንዲያስቡ በማድረግ ችግሩን ከምንጩ የማድረቅ ርምጃ ሊሆን ይችላል።

ይህን ተፈጻሚ ለማድረግ ኢትዮጵያ ያለችበት የፖለቲካ ነባራዊ ሁኔታ ፈታኝ ሊሆን ይችላል። ግን ሕዝቡን የሰላም አቅም አድርጎ ማደራጀትና ለሰላሙ ዘብ እንዲቆም ማድረግ ከመንግስት የጸጥታና የደህንነት አካላት የሚጠበቅ ጥልቁ ስራ ነው ። የክልል መንግስታት እስከ ቀበሌ ባለው የስልጣን እርከን የሚገኙ የጸጥታ አካላት የስራ ሃላፊዎችን ቁርጠኝነት እንዲሁም የፖለቲካ ታማኝነት ፈትሸው ውስጣቸውን ከባንዳዎች ማጽዳት ለነገ የሚሉት የቤት ስራ መሆን የለበትም። በሁለት ቢላ ከሚበሉ አካላት የተነሳ ንፁሀን የነፍስ ገዳዮች አሰቃቂ ጥቃት ሰለባ መሆን የለባቸውም። ለዚህ ፈጥኖ መንቀሳቀስ ወሳኝ ነው ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

# የወቅትና ፋሽን ጥምረት

ተገኝ ብሩ

ፋሽን ከወቅት ጋር ያለው ቁርኝት እጅጉን የጠበቀ ነው። ዋነኛ የፋሽን ባህሪያት ከሆኑት ጉዳዮች ውስጥ ወቅታዊነት አንዱ ነውና ዘመን፣ ቦታና ሁኔታ የሚሉት ጉዳዮች ይገለጡበታል። አንድ ፋሽን በየትኛው ዘመን በነበሩ ሰዎች ይዘወተራል፣ አልባሳት ከሆነ በየትኛው ወቅት ይለበሳል ወይም መዋቢያ ይሆን ነበር። የትኛው ቦታና በምን ሁኔታስ ይዘወተር ነበር? የሚሉት ጥያቄዎች ፋሽን ከወቅት ጋር ያለውን ጥብቅ ትስስር በግልጽ የሚያመላክቱ ናቸው።

ለዚህም ነው አንድን ፎቶ ግራፍ ወይም ተንቀሳቃሽ ምስል ስንቃኝ፤ ከአለባበሱ ተነስተን በየትኛው ዘመን ላይ እደነበር ለመገመት የምንችለው። በዚያን ወቅት ብዙ ሰዎች የሚያዘወትሩትና አምረው ተውበው ይታዩበት የነበረውን ፋሽን ተመርኩዘን ከዘመኑ ጋር እናስተሳስረዋለን። አለባበስ ብቻም ሳይሆን የጸጉር ቁርጥና አሰራር፣ የሜካፕ አጠቃቀምና አጋጌጥም፤ ዘመን በፋሽን ውስጥ በተለየ መልክ እንደሚታይ፣ ፋሽንም በዘመን ውስጥ የሚያልፍና የሚቀያየር ለመሆኑ ማሳያ ናቸው።

አንድ ፋሽን በፋሽንነቱ ተለምዶ በብዙዎች ይዘወተር ዘንድ መነሻ የሚሆኑ በርካታ ምክንያት ይኖሩታል። መቼና የት ተፈጠረ? እንዴትስ ተስፋፋ? የሚሉት ጥያቄዎች ደግሞ ለዚህ ምላሽ ይሆናሉ። አሁን አሁን ብዙዎቻችን አውቀን አልያም ሳናውቀው የፋሽን ዘርፉ ተካፋይና በፋሽን አልባሳት የምንዋብ ሆነናል። ወቅቱን ጠብቀን ሽክ ማለት፣ የአየር ጠባዩንም ለይተን በመልበስ ማጌጥና መዘነጥ እያዘወተርን ነው። የክረምት ወቅትን ደረብረብ አድርገን ብርዱን የተከላከልንበትንና ወፍራም ገበር ያለውን ሙቀት የሚጠብቅ ልብስ፤ የጸደይ ወቅት ብቅ ሲል መቀየር የግድ ይለናል።

በጋ ላይ ደግሞ ሙቀትን የሚቋቋም ሳሳ ያለ፣ ከቅለቱ ባሻገር ስንለብሰውም የሚያዘንጠንን ልብስ ከመደርደሪያችን መምረጥ፤ ከሌለንም ወደ መሸጫ ሱቆች ጎራ ማለታችን አይቀርም። ወቅት ለፋሽን መለያ ባህሪው ነውና በእርግጥም ወቅቱን መምሰል ራሳችንን ከሁኔታዎች ጋር ከማዋደዱም ባለፈ ዘናጭና ከጊዜው ጋር የምንራመድ ያደርገናል።

ወቅት ከፋሽን ጋር ያለው ጠንካራ ቁርኝት በሌሎች ጉዳዮች እንደሚወሰንም የዘርፉ ባለሙያዎች ያስረዳሉ። ባህል፣ እምነት፣ የአኗኗር ሁኔታ፣... ከተጽዕኖ አሳዳሪ ምክንያቶች መካከል ተጠቃሽ ናቸው። ምን በምን አይነት ቦታዎች ላይ ይለበሳል የሚለውን ጨምሮ፤ የዘወትር፣ የበዓል አሊያም ሁነቶችንም መሰረት ያደርጋል። ቀን፣ ማታ፣ ጸደይ፣ በጋ፣ ክረምት የመሳሰሉትም እንደ አየር ንብረቱና ወቅቱ አለባበሳችንን ሊወስኑ ይችላሉ። ፋሽንም እነዚህን መሰረት አድርጎ፤ የማህበረሰቡን ባህል፣ እምነትና ልማድ መሰረት ባደረገ መልኩ ይተገበራል።

የፋሽን ዲዛይነርዋ ስምረት ኃይሌ ለሁለት ዓመት በፋሽን ዲዛይን ሙያ ስትሰራ ቆይታለች። ባለሙያዋ ከአየር ንብረት ጋር የሚሄድ ሲለብሱት እና ሲያጌጡበት ከሰውነት ቅርጽና የአለባበስ ምርጫ ጋር የሚሄድ ፋሽን መከተል የሰዎች ተለምዷዊ ተግባር እየሆነ መምጣቱን ትናገራለች። ማህበረሰባችን ለፋሽን ያለው ምልከታ እያደገ መሆኑን የምታስረዳው ዲዛይነር ስምረት አቅም በፈቀደ መልኩ ወቅቱን እና የአየር ንብረቱን ያገናዘበ አልባሳት በተለይም በከተሜው ዘንድ መለመዱን ታስረዳለች።

ከወቅቱ የአየር ንብረት ጋር ከመስማማቱም ባሻገር ፋሽን በብዙዎች ተመርጦ የሚለበስና የሚዘወተር ሲሆን፤ በወቅቱ ገኖ እንዲወጣ የሚደርገው ግን አልባሳቱን የሚለብሰው ማህበረሰብ ባህል ጋር የማይቃረን ከሆነ ብቻ ነው። ለምሳሌ ዲዛይነሮች የበጋ ወቅት ቀለል ያሉ አልባሳትን ሲያዘጋጁ ወቅቱን ብቻ ሳይሆን ባህሉንም መሰረት ያደረገ ቢሆን ለፈጠራቸው ተቀባይነት አስተማማኝነቱ የቀረበ እንደሚሆን ዲዛይነር ስምረት ታነሳለች። ስለዚህ ባህልም እንደ ወቅት ሁሉ ፋሽን ላይ ትልቅ ሚና ይጫወታል ባይ ናት።

ፋሽን ወቅት መሰረታዊ ጉዳዩ ነው የምትለው ባለሙያዋ ይህንን ያገናዘበ፣ ተወዳጅ የሆነ ቀለምን የተላበሰ፣ በጥሩ ዲዛይነር ባማረ መልኩ ተሰናድቶ ለህረተሰቡ ሲቀርብ የማይወደድበት ምክንያት ፈጽሞ እንደማይኖርና የዲዛይነሮች ትኩረትም ምን መሆን እንዳለበት ታስረዳች። በመሆኑም ከላይ ያሉትን ቅድመ ሁኔታዎች አሟልቶ ከለባሹ ማህበረሰብ ባህል ጋር ከተሳካ ወይም ከገጠመ ልብሱ በሌሎች እንዲወደድና በብዙዎች እንዲለበስ ምክንያት እንደሚሆንም ባለሙያዋ ጨምራ ታመላክታለች።

ልክ እንዳሁኑ ቅዝቃዜ ባለበት ወቅት ሰውነትን በሙሉ ሸፍኖ ብርድን የሚከላከልና የሰውነት ሙቀትን የሚጠብቁ በአብዛኛው ከጥጥ የተሰሩ ወፍራም ልብሶች በብዙዎች የመመረጡን ያህል፤ ወቅቱ በበጋ ሲለወጥ ደግሞ በአብዛኛው ቀለል ያሉ፣ ሙቀትን ሊቋቋሙ የሚችሉ፣ በቀለማቸው ፈካ



ያሉና ከሰውነት አቋምና ቅርፅ ጋር የሚስተካከሉ አልባሳቶች በብዙዎች ይዘወተራል።

በእርግጥ እንደ ሰው ፍላጎትና የአለባበስ ምርጫ ቢለያይም ወቅቱን ባገናዘበ መልኩ ለመዋብ ሁሉም የበኩሉን ጥረት ያደርጋል። ከወቅቱ ጋር የሚሄዱ አልባሳት መልበስ አንድም በምርጫ ሲሆን ሌላኛው ጉዳይ ደግሞ ተፈጥሮ በራስዋ ታስገድዳለች። የሞቀው ሙቀቱን ሊከላከልለት የሚችል ልብስ የበረደውም ሰውነቱ በብርድ እንዳይጎዳና ስሜቱ እዳይረበሽ የሚያስችለውን ልብስ ለመልበስም ይገደዳል።

ማህበረሰባችን በተለያየ ጊዜ የራሱን አስተሳሰብና ባህላዊ ገጽታ የሚያንጸባርቁ አልባሳት ፋሽን አድርጎ ሲከተል ይታያል። ወጣቱ ዲዛይነር ሳምሶን በላይ ማህበረሰባችን ለወቅታዊ አለባበስ ያለው አጠቃላይ ምልከታ ምን ይምስላል ለሚለው ጥያቄ ምላሹ እንደሚከተለው ነው። አሁን ላይ ማህበረሰባችን በተለየ መልክ ፋሽን ተከታይ እየሆነ ነው የሚለው ሳምሶን እንደ ወቅቱ ዘንጦና አምሮ መታየት የሚያዘወትረው በርክቷል ይላል። የመግዛት አቅም ካልወሰነው በቀር፤ ወቅታዊና ከአየር ንብረቱ ጋር የሚሄድ እንዲሁም ለሰውነት ምቹ የሆነ ልብስ የመልበስ ፍላጎት እንዳለውም ምልከታውን ያጋራል።

እንደ ዲዛይነር ሳምሶን ገለጻ፤ ምንም እንኳን በዚህ ጊዜ ፋሽን እጅግ የተጋነነበትና ፈጣን መለዋወጥ የሚታይበት ቢሆንም እንደኛ ማህበረሰብ ወቅቱን በጠበቁ አልባሳት መዋብ እየተለመደ ነው። በዚህም ፋሽንና ወቅታዊ የአለባበስ ልምዶች አሁን ላይ እየተለመደ እንደሆነና ማህበረሰባችን የፋሽን ተከታይነቱን እንደሚያመላክትም ይገልጻል። ለዚህም ዘርፉ ያለውን ዕድገትና ለውጥ በማሳያነት ይጠቅሳል። ወጣቶች አሰርተው የሚለብሱዋቸው ልብሶች አልያም በራሳቸው ምርጫ ከልብስ መሸጫ መደብሮች ገዝተው የሚለብሱዋቸውና የሚጫሟቸው አዳዲስ ዲዛይን ልብሶች ለዚህ ማሳያ መሆኑንም ያስቀምጣል።

# ማረፊያ/ትዝብት

# በቤት የሌለውን በአደባባይ መፈለግ

አቤል ገ/ኪዳን

መቼም ማህበራዊ ሚዲያ የማያሳየው ጉድ የለም። ለብዙዎች የነጻ ንግግር መብታቸው እንዲከበር ያደረገውን ያህል በዚያኑ ልክ የብዙዎቹ ድብቅ አሉታዊ ባህሪ ጎልቶ እንዲወጣም አድርጓል። ከሁሉ በላይ ግን ጎልቶ እንዲወጣ ያደረገው በሁላችንም ውስጥ የተደበቀውን የአምባገነንነት ባህሪ ነው። ይህን ያልኩት ያለ ምክንያት አይደለም። የሰሞኑን የማህበራዊ ሚዲያ ውይይታችንን አስተውዬ ነው።

ሁላችንም እንደሰማነው አርቲስት አቤል ሙሉጌታ አዲስ ነጠላ ዜማ አውጥቷል። የሙዚቃውን ይዘት አልተነትንም። ነገር ግን ሙዚቃው በዩቱብ ከተለቀቀ በኋላ ከስር ስለሙዚቃው የተሰጡ አስተያየቶችን ያየ ሰው መደንገጡ የማይቀር ነው። ህዝባችን ይሳደበዋል አይገልጸውም። የስድቡ እና የእርግማኑ አይነት እጅን በአፍ ያስጭናል። ልብ አድርጉ መቃወም መብት ነው። በመቃወም እና በመሳደብ መካከል ግን ሰፊ ልዩነት አለ። የብዙዎች ተቃውሞ ሳይሆን ስድብ ነው። ስድቡ ደግሞ አጸያፊ ከመሆኑ የተነሳ ይሄ ስድብ ሀይማኖተኛ ነው ከሚባል ህዝብ የሚወጣ አይመስልም። ያሳፍራል። የበለጠ አሳፋሪው ነገር ደግሞ ድምጻዊውን ሆን ብሎ ለመጉዳት ከዚህ ዓለም በሞት የተለየች ባለቤቱን ታሪክ በስድብነት ሲጠቀሙ መስማት ነው። ይህ ጸያፍ ነው። ይህ ነውር ነው። ይህ ክብረ ነክ ነው።

የሚገርመው ነገር ህዝባችን ስለ ነጻነት ሀሳብን መግለጽ ሲሟገት በጣም ሀይለኛ ነው። ሁሌም መንግስትን የሚተቸው በዚህ ነው። እገሌ ብእር ብቻ ነው የያዘው ፤ ብእር የያዘን ሰው ማሰር ፍርሀት ነው ምናምን ይልሀል። ነገር ግን የመናገር ነጻነትን በመቀማት ከመንግስት ይልቅ ማህበረሰቡ ራሱ ይቀድማል። ሁሉም ሰው የመናገር ነጻነት መከበር አለበት ብሎ የሚያምነው እሱ ሲናገር ወይም እሱ ሊናገር የፈለገውን ሌላ ሰው ሲናገርለት ነው። ከዚያ ውጭ የመናገር ነጻነት እሱ መስማት ለማይፈልገውም ሀሳብ እንደሚሰራ አይገነዘብም ወይም ሆን ብሎ ይክዳል። ይሄ የማህበራዊ ሚዲያ እንቅስቃሴያችን ያጋለጠው ሀቅ ነው።

ዲሞክራሲ በባህሪው ከስር እየተገነባ የሚሄድ እንጂ ከላይ የሚሰጥ አይደለም። እኛ ግን ከቤታችን ያላሳደግነውን ዴሞክራሲ ነው ከመንግስት ቢሮ የምንፈልገው። ቤቱ እየተኮረኮመ ያደገ ሰው ቢሮ ሄዶ በነጻ ሀሳብ የሚያምን ይሆናል ማለት ዘበት ነው። ህዝብ እርስ በርሱ አንዱ ሌላውን በሀሳብ እየሞገተ ሲያድግ ዴሞክራሲ ያብባል አልያ ግን አንዱ ሌላውን እየጠለፈ እና እያሸማቀቀ የሚቀጥል ከሆነ ዴሞክራሲ እንኳን ሊያብብ እንዲያውም ለአምባገነን መንግስት መፈጠር በር ሊከፍት ይችላል።

እርግጥ እንደ ህዝብ ካሉብን ችግሮች መካከል እኛ ሊኖረን የሚገባውን ነገር በሙሉ ከመንግስት መጠበቅ አንዱ ነው። ለምሳሌ ያህል የትምህርት ጥራት እንዲሻሻል እንፈልጋለን። ነገር ግን የልጆችንን ደብተር ለማየት ፤ የቤት ስራ ለማሰራት ፤ ለማስጠናት ፍላጎት የለንም። የትምህርት ጥራት ግን የብዙ ነገር ድምር ውጤት ነው። ካላስጠናን ፤ የቤት ስራ ካላሰራን፤ አጋዥ መጽሀፍትን ካላቀረብን ፤ እንዳይርባቸው ካላደረግን ፤ አእምሯቸው ትምህርት ላይ ብቻ እንዲያተኩር ካላገዝን ፤ ውሏቸውን ካልተከታተልን ልጆች ትምህርት ቤት ውስጥ ብቻ በሚደረግ ስራ ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉም። ያን ሳናደርግ ግን ስለ ትምህርት ጥራት ብናወራ ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ የሚለው ተረት በኛ ላይ ይፈጸማል።

ሁላችንም ፍትህ እንዲሰፍን እንፈልጋለን። ፍርድ ቤት እኛ በምናውቃቸው ሰዎች ላይ የሚወስነውን እያንዳንዱን ውሳኔ እንከታተላለን ፤ የፖሊስን ችግር እንነቅሳለን ፤ አቃቤ ህግ ብዙ ችግር እንዳለበት እንዘረዝራለን። እኛ ያለ ጥፋታቸው ታስረዋል ለምንላቸው ሰዎች እንዲህ ስንሟገት ላየን ሰው ስለ ፍትህ ያለን ተቆርቋሪነት በጣም ከፍተኛ ሊመስለው ይችላል። ነገር ግን በዚያው ልክ ባለስልጣን ዘመድ ካለን ተማምነን ኢ ፍትሀዊ ነገር ስናደርግ ቀዳሚዎቹ እኛ ነን። ለፖሊስ እና ለአቃቤ ህግ ጉቦ ሰጥተን ክስ ስናዘጋም ማንም አይበልጠንም። ሌላም ሌላም። እኛ በግላችን ጉዳይ የማናደርገውን ነገር መንግስት ግን ወንጀል ፈጽመዋል በሚላቸው ሰዎች ላይ እንዲፈጽም እንጠብቃለን።

ወደ ቀደመው ጉዳይ እንመለስና አሁንም ስለ አቤል ሙዚቃ እና ስለ ዴሞክራሲ እናውራ። በመሰረቱ ለአንድ ድምጻዊ ምን መዝፈን እንዳለበት መወሰን ያለበት ማነው? ራሱ ድምጻዊው ብቻ አይደለምን፣ መሆን ያለበትም እንደዛ ነው። ድምጻዊው ያሰኘውን ይዘፍናል ፤ ህዝብ የሚጥመውን መርጦ ይሰማል። ድምጻዊው ምን መዝፈን እንዳለበት ማንም ሊነግረው አይገባም ፤ ህዝብም ምን ማድመጥ እንዳለበት ሊወሰንለት አይገባም። ድምጻዊም ምን መዝፈን እንዳለበት እና መቼ መዝፈን እንዳለበት እንወስን ካልን ግን ወደ ሳንሱር ዘመን ተመለስን ማለት ነው። ለመሆኑ አቤል በዘፈነው ሙዚቃ ላይ መንግስት አልጣመኝም ብሎ በቁጣ የተሞላ መግለጫ ቢያወጣ ተቀባይነት አለው የለውም?። ልክ እንደዛው የብዙዎቻችን ስድቦችም ተቀባይነት የላቸውም።

ደግሞ በጣም አስነዋሪ ነገር አንድን ሰው ለሰራው ስራ ቤተሰቡን አብሮ የመውቀስ አዲስ ባህል ነው። ይህ በጣም አስነዋሪ ነው። ልጅን በአባቱ ጥፋት መውቀስ ፤ ሚስትን በባሏ ጉዳይ መተቸት ፤ እህትን በወንድሟ ጉዳይ ማንጓጠጥ በጣም ጸያፍ ልማድ ነው። ይሄ ኢትዮጵያዊ ባህሪ አይደለም። እንኳን በዚህ ዓለም በህይወት የሌለችን ሴት ቀርቶ በህይወት ያለችውንም ቢሆን እሷ በሌለችበት ባላረገችው ጉዳይ ስሟን ማንሳት አስነዋሪ ባህሪ ነው። በአቤል ሙዚቃ ጉዳይ ባለቤቱን ማንሳት የህሊና ቢስነት መገለጫ ነው።

ልብ አርጉ ፤ የምንከራከረው ስለ አቤል ሙሉጌታ አይደለም። የምንከራከረው በህዝብ ደራጃ እያዳበርነው ስለመጣነው አምባገነንነት ነው። ይህ አዲስ ባህል አደገኛ ነው። አምባገነን ህዝብ ዴሞክራሲያዊ መንግስት አይኖረውም። በፌስቡክ ላይ የሌለውን ዴሞክራሲያዊ ውይይት በምክር ቤት ልናገኘው አንችልም። የሰሞኑ ጫጫታ ያመላከተው ነገር ቢኖር ግን እኛ ራሳችን በነጻነት ሀሳብን የመግለጽ መብትን እያፈንን መንግስት ግን እንዲያከብር እና እንዲያስከብር እንደምንፈልግ ነው።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# በአንድ አይነት ግጥም እና ዜማ ስለሀገራችን የምንዘምርበት ጊዜ ላይ ነን!

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

የኢትዮጵያ ታሪክ በብሄርና በጎሳ ቁርሾ ተጀምሮ ያቆመበት ጊዜ ላይ ነን። የኢትዮጵያ ታሪክ ፖለቲካ ወለድ በሆነ ጦርነትና አለመግባባት ተጀምሮ የቆመ ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ ፍቅርና አንድነት በማጣት ያደፈበት ጊዜ ላይ ነን። የኢትዮጵያ ታሪክ የአንድነት ክንድ አጥቶ የሰለለበት ጊዜ ላይ ነን። በዚሕ የተነሳ እራሴን ጨምሮ ዜጎችን---መንግስትን..ፖለቲከኞችን ከትናንት የታሪክ ምእራፍ መረማመጃ ድልድይ መስራት እንዴት አቃተን ብዬ ለመጠየቅ ውስጤ ይነቃቃል ።

የቀደመውን በሰላም በፍቅር ተሳስቦና ተቻችሎ ለመኖር በፍቅርና በይቅርታ፣ በእርቅና በድርድር የተገነባ ትውልድ የሚረማመድበትን ድልድይ መስራት ይኖርብናል። ይሄን ታሪክ ለማደስ በምክክርና በተግባቦት የታነጸ ከዚህ ወደዚያ መራመጃ የብረት ድልድይ ያሻናል። እግሮቻችን በጽናት የሚቆሙበት መረማመጃ ሳይኖረን ሀገር ማሻገር አይቻለንም።

በመካከላችን ያለውን የልዩነት ሽል አምጠን መውለድ አለብን። ወደ ፊት እንዳንሄድ ያደረገንን የጎጠኝነት ሀሳብ ገለን መቅበር አለብን። ችግሮቻችንን በጋራ አምጠን፣ በጋራ በመውለድ የሚያድገውን አሳድገን፣ የሚሞተውን ገለን የአንድነት ድልድይ መገንባጽ ለህልውናችን መሰረት ነው ።

ችግሮቻችንን በጋራ የማሸነፍ ክህሎት እስካላዳበርን ድረስ በቆፈርነው ጉድጓድ ውስጥ ከመውደቅ ሌላ አማራጭ የለንም። ለነገሩ አሁንም እየወደቅን ነው። ትላንትና ሌሎችን ለመጣል ያጠመድናቸው የፖለቲካ ወጥመዶች እኛኑ እያሰቃዩን ነው። የተበተብናቸው የማስመሰል አካሄዶች ዛሬ ላይ በአያሌው እያሰቃዩን ነው።

ከነበርንበት፣ ከኖርንበት የፖለቲካ አስተሳሰብ መውጣት አለብን። ኢትዮጵያን አይታችኋት ከሆነ እየተሰቃየች ያለችው በፖለቲከኞቻችን ነው። ህዝባችንን አይታችሁት ከሆነ መከራ እያየ ያለው በፖለቲከኞቻችን ራስ ወዳድነት ነው። ከከተማ ወጣ ብሎ ያለው ኢትዮጵያዊነት፣ ያለው መተሳሰብ የሚደነቅ ነው ። ኢትዮጵያዊነት የቆሸሸው ከተማ ውስጥ ነው። እያበላሹን ያሉት ፖለቲከኞቻችን ናቸው። ከሁሉ በፊት የፖለቲካውና የፖለቲከኞቻችን እድፍ ሊጠራ ይገባል።

በቀደሙት ዘመናት እልህና አልሸነፍም ባይነት ዋጋ እያስከፈሉን ኖረዋል። አሁን ጊዜው ስለኢትዮጵያ የምንኖርበት ነው። ለዘመናት ስለራሳችን ኖረን አይተነዋል። እስኪ ደግሞ ስለኢትዮጵያዊነት እንኑርና እንየው። እስከመቼ አድሮ ቃሪያ እንሆናለን? ጦርና ጐራዴዎቻችን ጊዜ የሚያልፍባቸው መቼ ይሆን? በኢትዮጵያ ምድር በሀሳብ ማሸነፍ፣ በንግግር መርታት መፈጠሪያቸው መቼ ይሆን? በአንድ አይነት ፖለቲካ፣ በአንድ አይነት ሀሳብ፣ በአንድ ወጥቶ መግባት ሀምሳ አመታትን ደፈንን። መች ይሆን ትንሳኤያችን?

ብዙ እያወቅን፣ ልንማርባቸው የምንችልባቸው ብዙ ትላንትናዎች እያሉን ለምን የተሻለ ሀገርና ህዝብ መፍጠር አቃተን ? በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ቅርሶች ተከበን፣ ሰፋፊና ለም መሬቶችን ታቅፈን፣ የሚሰሩ እጆች፣ የሚያስቡ ጭንቅላቶች ሞልተውን ለምን ግራ ተጋባን ? በታሪክ ልቀን፣ በባህል ደምቀን ለምን ጨለማ ውስጥ ለመኖር ተገደድን ? ብዙ የተማሩ፣ ብዙ ፊደል የቆጠሩ ምሁራን እያሉን ለምን በድንቁርና መንገድ ላይ ቆምን ? ከሁሉም ትልቁ ፍቅር ስለሌለን ነው።

የህግ ሁሉ ፍጻሜ የሆነው ፍቅር ልባችን ውስጥ ስለሌለ ነው። ተነጋግሮ መግባባት ስላቃተን ነው። ሰው ተነጋግሮ መግባባት ካቃተው ለለውጥ የሚሆን ሀይል አያገኝም። ሰው ተነጋግሮ መግባባት ካልቻለ እውቀቱ፣ ጥበቡ ሁሉ ጥቅም መስጠት ያቆማሉ። ሰው ለራሱም ሆነ ለሌሎች አደገኛ መሆን የሚጀምረው በዙሪያው ካሉ ሰዎች ጋር መግባባት

> **ፈተኝነት እንደናፈቀን እንዳይቀር ከኋላ ያስቀሩንን ችግሮቻችንን አሸንፈን መቆም ይጠበቅብናል። የጥንቱን የአንደኝነት ክብራችንን ለመመለስ ብሄርን ሳይሆን ሰውነትን ያስቀደመ የፖለቲካም ሆነ የማህበራዊ እሴት ያስፈልገናል**

ያልቻለ ቀን ነው። ሰው ከሰውነት ወደ አውሬነት የሚቀየረው በውስጡ ተናግሮም ሆነ አድምጦ ከሰዎች ጋር መታረቅ ሳይችል ሲቀር ነው።

ሰው ከእንስሳት የሚለየው ማሰብ በመቻሉ ነው። የማሰብ የመጀመሪያው ምዕራፍ ተነጋግሮ መግባባት ነው። የማሰብ የመጀመሪያው ገጽ በላሸቀ ሀሳብ የተፈጠሩ ችግሮችን በላቀ ምክረ ሀሳብ መፍታት ነው። ተነጋግረን ካልተግባባን መማራችን፣ ማወቃችን ጥቅሙ ምን ላይ ነው? ሰው የሚማረው እኮ ህይወቱን ቀላል ለማድረግ ነው። ትምህርት ከሌሎች ጋር አግባብቶ ህይወታችንን ካላቀለለልን መማራችን ዋጋ አይኖረውም። የሰው ልጅ በበላጭ ሀሳብ፣ በምክንያታዊነት ከሌሎች ጋር ተነጋግሮ ካልተግባባ ሰው ሊባል አይችልም። ምክንያቱም ሰውነት ከማሰብ ጀምሮ ወደ ላቀ የማንነት እርከን የሚሸጋገር ስለሆነ ነው። እኛ ግን ከዚህ ውጪ በሆነ የኑሮ ዘይቤ መከራችንን እያየን ነው።

ባለመግባባት መግባባት የሚፈጥርልንን መልካም እድል ማየት አልቻልንም። አሁን እኛ ባለመነጋገር መነጋገር የሚፈጥርልንን ሀገራዊ በረከት መቋደስ አልቻልንም። በጸለምተኝነት ብርሀናዊ ጎዳናችንን እያጸለምን ነው። ድልድይ እንስራ..ከዚህ እዚያ መሻገሪያ ድልድይ እንገንባ። በሀሳብ ተላቁጦ በአንድነት የተዋሀደ፣ በብዙ ምክረ ሀሳብ የጠነከረ የብረት መረማመጃ እንገንባ።

‹ሰው ከእንስሳት የሚለየው ማሰብ በመቻሉ ነው› የሚለው ይህ የልጅነት ጥበባችን ወረቀት ላይ ካልሆነ በስተቀር እኛ ላይ ነፍስ ሲዘራ አይታይም። በማሰብ የተራመድንው ጎዳና የለም። ችግሮቻችንን ስናስወግድ የነበረው በሀይልና በመገፋፋት ነበር። ሀይልና መገፋፋት ደግሞ የማሰብ መገለጫዎች አይደሉም። ማሰብ ሁልጊዜም መፍትሄ ነው የሚሰጠን። ማሰብ ሁልጊዜም ምክንያታዊነትን ነው የሚያላብሰን። ራሳችንን በሀሳብ እንገንባ። የሀገራችንን መሰረት በእርቅና በምክክር እናጽና። በማሰብ የተገነባ ሀገርና ትውልድ ለጦርነት የሚሆን ጊዜ የለውም።

በማሰብ የተገነባ ትውልድ ለፖለቲካም ሆነ ለማናቸውም ነውጠኛ ሀይሎች እጅ አይሰጥም። ሀገራችንን ያራቆትናት እኛው ነን። አባቶቻችን ያለበሷትን የክብር ዘውድ የነጠቅናት እኛ ነን። አባቶቻችን ያጎናጸፏትን የአንድነት ካባ ያወለቅነው እኛ ነን። እስኪ ለአፍታ ትላንትን መለስ ብላችሁ ተመልከቱት..ምናችንም እኮ አባቶቻችንን አይመስልም። ሰው እንዴት ከጀግና አብራክ፣ ከኩሩ ጉያ በቅሎ ሌላ ይሆናል? ሰው እንዴት በአንድነት አፍሪካን ፈጥሮ፣ አለምን አነቃንቆ አጠገቡ ካለ ወንድሙ ጋር አይጥና ድመት ይሆናል? እኛ ከአባቶቻችን ጋር ዱባና ቅል ነን። አባቶቻችንን እስካልመሰልን ድረስ የክብር፣ የስልጣኔ፣ የታሪክ ሀይል አናበጅም።

እንደ ሳምሶን አናት ሀይላችን የአባቶቻችን አንድነት ነው። እንደ ሙሴ በትር ክብራችን የአባቶቻችን ስርዐት ነው። ሳምሶን እግዚአብሄር አምላክ በቀባው ጸጉሩ ላይ ምንም ነገር የማድረግ ሀይል ነበረው። ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብጽ ባርነት ሲያወጣ በበትሩ ላይ የእግዚአብሄር ሀይል ነበር። የእኛም ሀይል የአባቶቻችን የአንድነትና የወንድማማችነት መንፈስ ነው። የሳምሶን ሀይል የደከመው፣ ሳምሶን ሀይሉን ያጣው ክብሩን የትም ጥሎ በደሊላ የተረታ ቀን ነበር።

የእኛም ሀይል፣ የእኛም ክብር እያደፈ ያለው የአባቶቻችንን የአንድነት መንፈስ በብሄርና በጎሳ የመነዘርን ሰሞን ነው። ሳምሶን ወደ ክብሩ ይመለስ ዘንድ እግዚአብሄርን ማወቅና ወደ እሱ መመለስ ግድ ይለዋል። እኛም ወደ ቀደመ ክብራችን እንመለስ ዘንድ የአባቶቻችንን የፍቅር ልብሰ ተክህኖ መልበስ አለብን። ያለዛ በባዶ ሜዳ እዬዬ ከማለት በስተቀር የምንቀይረው አንዳች ነገር አይኖርም።

ለውጥ ፍቅር ይፈልጋል። ፖለቲካ መነጋገር፣ ተነጋግሮም መግባባት ግድ ይለዋል። አብዛኞቹ የፖለቲካ ጽንሰ ሀሳቦች ሀገርና ህዝብን መሰረት ያደረጉ ናቸው። በዚህ ጽንሰ ሀሳብ ውስጥ እውቅና ያገኙት ሀገርና ህዝብ ደግሞ ተግባቦትን መርህ ያደረገ፣ ንግግርን እንደ ፖሊሲ የቀረጸ መንግስታዊ ስርዐት ይፈልጋሉ። ይሄ ሁሉ ባልሆነበት ሁኔታ ውስጥ የምንፈጥረው የጋራ ታሪክ አይኖረንም።

ባለማሰብ ውስጥ መቆም ባለመግባባት ውስጥ መፈጠር ነው። አለማሰብ ሁልጊዜም መድረሻው ጦርነት ነው። እስካሁንም እንደ ሀገር የፈጠርናቸው ችግሮቻችን ባለማሰብ የቃኘናቸው ስለሆኑ ነው። ለምንም ነገር የሰከነና አርቆ የሚያይ ልቦና ያስፈልገናል። ችግሮቻችንን ችግር በሚፈጥር ሀሳብ ሳይሆን ሰላም በሚያመጣ ሀሳብ ማሸነፍ መልመድ አለብን። ይሄን ሳናደርግ ፈተኝነት የማይታሰብ ነው። ነጋችን እንዲያብብ ዛሬ ላይ ምርጥ ዘሮች እንሁን።

ጥሩ ዘሮች ጥሩ አበባና ጥሩ ፍሬ ከመሆን ሌላ አማራጭ የላቸውም። የእኛም አማራጭ ሊሆን የሚችለው ጥሩ ዘሮች በመሆን ለትውልዱ ሰላሳና ስልሳ መቶም ማፍራት ነው። ነገ ላይ ትውልድ የሚጠረጥረው የእኛን የዛሬ ፍሬ ነው። ነገ ላይ ትውልዱ ገልጦ የሚያነበው የእኛን የዛሬ ታሪክ ነው። ነገ ላይ ትውልዱ ቀና የሚለው ወይም አንገቱን የሚደፋው በእኛ የዛሬ ሀሳብ ነው። የሀሳብ ፍሬአችን ነገ ለሚፈጠረው አዲስ ትውልድ የበረታ ጉልበት አለውና ሰው መሆን ይጠበቅብናል ። በሀሳባችን የትውልዱን ድልድይ እንገንባ። በተግባራችን ለሌሎች ድልድይ እንሁን። በእርቅና በተግባቦት የተጠረገ፣ ከዛሬ ወደ ነገ መሄጃ መንገድ እስካልሰራን ድረስ ከመተቻቸትና ከመነቃቀፍ አንወጣም።

ከጥንት እስከዛሬ የሀገራችን ስቃይ መነሻው ፖለቲካ ነው። ፖለቲካው የማይገባበት የማህበረሰብ ክፍል ስለሌለ እድፉ አይለቀንም። ይሄን እድፍ እናጠራ ዘንድ ብሄራዊ ምክክር አስፈልጓል። የብሄራዊ ምክክሩ ዋና አላማ በጋራ ሀሳብ የጋራ ሀገር መፍጠር ነው። በጋራ ሀሳብ የጋራ ሀገር ለመፍጠር ደግሞ በፖለቲካም ሆነ በሌላ ምክንያት የተበላሹ ችግሮቻችንን የምናሸንፍበትን የበረታ ሀሳብ ማዋጣት ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል። ባለፉት ሀምሳ አመታት ውስጥ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ብዙ ችግሮችን ፈጥረናል። እነዚህ ችግሮች ፈረሰው ድልድይ እንሰራ ዘንድ ሀገራዊ ምክክር የግድ ይላል። ሀገራችንን እያሰቃያት ያለው እንዲህ አይነቱ በሀሳብ አንሶ በችግር የመላቅ አባዜ ነው።

በሀሳብ አንነስ ..በሀሳብ የምናንስበት ጊዜ ያበቃል ፤ ምክንያቱም የሀገራዊ ምክክሩ አላማ በሀሳብ የላቀ ማህበረሰብ መፍጠር ነው። ከትላንት ጀምረን እሹሩሩ ስንላቸው የነበሩ ችግሮች አሉ። ከማን እንደጸነስናቸው ሳናውቅ በውሸት ያረገዝናቸው፣ አርግዘንም የወለድናቸው፣ ወልደንም እያረስናቸው ያሉ ዛሬ ላይ እኛኑ እያጠቁን ያሉ ችግሮች ግብዐተ መሬታቸውን ለማፍጠን ያለን አማራጭ መነጋገር ብቻ ነው።

ባለ ማሰብ፣ ባለመግባባት፣ ባለመነጋገር የአእምሯችንን በር ቆልፈን ጊዜ ያለፈባቸውን ድርጊቶች እየከወንን ጊዜው ያለፈበት ሀገርና ህዝብ ፈጥረናል። አሁን የምፈራው ለምንም የማይጠቅም ወደ ኋላ የሚያስብ ጊዜ ያለፈበት ትውልድ እንዳንፈጥር ነው። ሁሉም ነገር በእኛ እንዲበቃ ለሚመጣው ትውልድ ስንል መስዋዕት መክፈል አለብን። እኛ ላይ የሆነው የጦርነት፣ ያለመግባባት ስቃይ በልጆቻችን ላይ እንዳይደገም ዛሬ ላይ የእርቅ መሀላ እንፈጽም።

ሀሳብ በሀሳብ እንጂ በጦርነት አይሻርም። ሀሳቦቻችንን በሀሳብ የመምረጥ ጥበብን እንማር። ዛሬ ላይ ከተቀረው አለም በብዙ ነገር ወደ ኋላ ቀርተናል። ኢትዮጵያዊነት ያነጻውን የአባቶቻችንን የአንድነት ድልድይ ዛሬ ላይ በብሄር ሸር ሸረንዋል። የአባቶቻችንን የፍቅር ድልድይ ዛሬ ላይ በኔነት አፍርሰነዋል። የዛን ትውልድ የጽናት ድልድይ ባለመግባባት ንደነዋል። ወደ ድሮ እንመለስ ዘንድ የፍቅር አሻራ ያረፈበት የይቅርታ ድልድይ ግድ ይለናል።

በአንድ አይነት ግጥም፣ በአንድ አይነት ዜማ አንድ ላይ ሆነን ስለሀገራችን የምንዘምርበት ጊዜ ላይ ነን። ፈተኝነት እንደናፈቀን እንዳይቀር ከኋላ ያስቀሩንን ችግሮቻችንን አሸንፈን መቆም ይጠበቅብናል። የጥንቱን የአንደኝነት ክብራችንን ለመመለስ ብሄርን ሳይሆን ሰውነትን ያስቀደመ የፖለቲካም ሆነ የማህበራዊ እሴት ያስፈልገናል። አለም በየቀኑ ሌላ አይነት ናት..እኛ ግን ሁልጊዜም አንድ አይነቶች ነን። ለውጥ ደግሞ የተለየ መሆን ይፈልጋል..ከዘመኑ ጋር የዘመነ፣ ከጊዜው ጋር የተስተካከለ አእምሮና ልብ ይፈልጋል። አዲስ እንሁን።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ለግብርና ዘርፍ ተቋማዊ ችግሮች መፍትሄ የሰነቀው ተቋም

አንተነህ ቸሬ

አብዛኛው ሕዝቧ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ኑሮው በግብርናው ዘርፍ ላይ የተመሰረተባት ኢትዮጵያ ከቀደመው ጊዜ ጀምሮ የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችሉ በርካታ ተግባራትን ስታከናውን ቆይታለች። በሀገሪቱ በመንግሥትና በዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች የተደገፉ ተከታታይነት ያላቸው የግብርና ልማት እንቅስቃሴዎች ተግባራዊ ተደርገዋል። ከእነዚህ እንቅስቃሴዎች መካከል በቀደሙት የመንግሥት ስርዓቶች የተተገበሩት የባለ ብዙ ዘርፍ የግብርና ልማት ማዕቀፍ ፕሮግራም (Comprehensive Agricultural Package Program) እና የግብርና ልማት ኤክስቴንሽን ትግበራ (Extension Program Implementation Department (EPID) እንዲሁም የቅርብ ጊዜዎቹ የኢትዮጵያ የልማት ፕላን መመሪያ ማዕቀፍ፣ የግብርና መር ኢንዱስትሪ ፖሊሲ (Agricultural Development Led Industrialization (ADLI)፣ የዘላቂ ልማትና ድህነት ቅነሳ ፕሮግራም፣ የመጀመሪያው እና ሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዶች (GTP I እና GTP 2) ተጠቃሽ ናቸው።

በእነዚህ የግብርና ዘርፍ ማሻሻያ መርሃ ግብሮችም በእርግጥ የአገሪቱን ምጣኔ ሀብት ያሳደጉና የሕዝቡን፣ በተለይም የአርሶ አደሩን፣ ሕይወት ያሻሻሉ ውጤቶች ተመዝግበዋል። ከግብርና የሚገኘው ምርት በየዓመቱ ጭማሪ ማሳየት ችሏል፤ እንደ ሀገር የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ተችሏል፤ ቁጥሩ ቀላል የማይባል የህብረተሰብ ክፍልም ከድህነት መላቀቁን መረጃዎች ያመለክታሉ። የግብርናና ገጠር ልማትን ለማሻሻል የተወሰዱ እርምጃዎች ብዙ ባለሀብት አርሶ አደሮችን መፍጠር ችለዋል።

ይሁን እንጂ እነዚህ ተግባራት ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ ካላት አቅም አንፃር ሲመዘኑ ለሀገሪቱ የምግብ ዋስትና፣ የስራ እድል ፈጠራና የምጣኔ ሀብት እድገትም ሆነ ለዘርፉ ችግሮች አስተማማኝ መፍትሄ የሰጡ አይደሉም። አሁንም ግብርናው በዘላቂነት ከኋላ ቀር አስተራረስና ከዝናብ ጥገኝነት አልተላቀቀም፤የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በብዛት ከመጠቀም የራቀ ሆኖ ይታያል። ሚሊዮኖች ከድህነት ወለል በታች እየኖሩ ነው። በአጠቃላይ መንግስት አቅዶት የነበውን የምጣኔ ሀብት መዋቅራዊ ለውጥን እውን ማድረግ አልተቻለም።

የግብርናውን ዘርፍ ችግሮች ለመለየት በመንግሥት ከተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች መካከል አንዱ ችግሮቹን የሚለይና ምክረ ሃሳቦችን የሚያቀርብ ተቋም ማቋቋም ነበር። በቅርቡ አደረጃጀቱ ወደ ኢንስቲትዩት የተቀየረው የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ (Ethiopian Agricultural Transformation Agency - ATA) የዚሁ የመፍትሄ እርምጃ አካል ነበር። የኢትዮጵያ ግብርና በበርካታ ችግሮች የተተበተበና ከግብርና የሚገኘው ውጤትም ከሀገሪቱ አቅምና ፍላጎት ጋር የማይመጣጠን በመሆኑ የዘርፉን ችግሮች ለመለየት ጥናት ተደርጎ፤ የተቋማት የመፈፀም አቅምና የቅንጅታዊ አሰራር ጉድለት እንዲሁም የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ችግሮች የዘርፉ ዋነኛ ማነቆዎች መሆናቸው በጥናቱ ማወቅ ተችሏል። እነዚህ ችግሮች እልባት ያገኙ ዘንድ ምክረ ሃሳብ የሚሰጥ ተቋም ያስፈልግ ስለነበር የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ተቋቋመ።

ኢንስቲትዩቱ በ2003 ዓ.ም ሲቋቋም በግብርናው ዘርፍ ያሉ ችግሮችን፣ በተለይም የአፈፃፀም ማነቆዎችን፣ በመለየትና ምክረ ሃሳብ በማቅረብ፤ በግብርናው ዘርፍ ተቋማት መካከል ቅንጅት እንዲፈጠር በማድረግ፤በፈጠራና ቴክኖሎጂ ለግብርናው ዘርፍ የእውቀት ማዕከል በመሆን፤ ሰርቶ ማሳያ ፕሮጀክቶችን በመተግበርና በመደገፍ እንዲሁም የአቅም ግንባታ ተግባራትን በማከናወን የግብርና ዘርፍ ሽግግርን የማሳካት ኃላፊነትን ይዞ ነው። እነዚህን ተግባራት በማከናወን ረገድም ብዙ ውጤቶችን አስመዝግቧል። በፖሊሲዎች እና በምርምሮች መካከል ያሉ የአሰራር ክፍተቶችን በመለየትና ምክረ ሃሳብ በማቅረብ የግብርና ባለድርሻ አካላትን ቅንጅት የሚስተባብረው ተቋሙ፣ በቅርቡ ደግሞ አደረጃጀቱን ወደ ኢንስቲትዩት በመቀየር የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት (Ethiopian Agricultural Transformation Institute - ATI) ሆኖ ተደራጅቷል።

የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ኡመር ሑሴን ኤጀንሲው/ አሁን ኢንስቲትዩት ተብሏል/ ባለፉት ዓመታት በግብርናው ዘርፍ ያሉ ክፍተቶችን በመለየትና ምርታማነትን በማሳደግ ረገድ ትልቅ አስተዋፅኦ ስለማበርከቱ ይናገራሉ። ለአብነት ያህል በአሁኑ ወቅት እስከ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት የመሸፈን አቅም መፍጠር በተቻለበትና በርካታ አርሶ አደሮችን ባሳተፈው የኩታ ገጠም እርሻ ዘርፍ ተጨባጭ ለውጥ መፍጠር መቻሉንና የኩታ ገጠም የአስተራረስ ዘዴን ተግባራዊ ያደረጉ አርሶ አደሮችን የምርታማነት ችግሮች ሊፈታ የሚችል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረጉን ይጠቅሳሉ። ተቋሙ በፖሊሲና በአሰራሮች ውስጥ ያሉ ችግሮችን የመለየትና መፍትሄ የመጠቆም ተግባራትን እንዳከናወነም ይገልፃሉ።

የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ማንደፍሮ ንጉሤ እንደሚሉት፣ ኢንስቲትዩቱ የግብርና ስርዓቱን ችግሮች በጥናት የመለየት፣ የአፈፃፀም ድጋፍ የመስጠት፣ ለዘርፉ ጠቃሚ የሆኑ ፕሮጀክቶችን በትግበራ እገዛ የማሳየት እና በእሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ተዋንያንን የማቀናጀት ተልዕኮዎችን ይዞ ሲሰራ ቆይቷል። ተቋሙ የዘርፉን ችግሮች በጥናት ከለየ በኋላ ምክረ ሃሳቦችንም ያቀርባል። ምክረ ሃሳቦቹ በባለድርሻ አካላት የማይተገበሩ ከሆነ የትግበራ ድጋፍ ይሰጣል።

በዚህ ሂደት ባለድርሻ አካላቱ ምክረ ሃሳቦቹን ለመተግበር ተጨማሪ አቅም ይፈጠርላቸዋል ማለት ነው። በመንግሥት ሊቀጠሩ የማይችሉ ከፍተኛ ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች በመቅጠር የምርምር፣ የግብይትና የኢንቨስትመንት ስራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ጥረት ያደርጋል። ለአብነት ያህል በግብርና ሚኒስቴር፣ በኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ በኅብረት ስራ ኮሚሽንና በሌሎች ተቋማት ውስጥ ሆነው የምርምር፣ የግብይትና የኢንቨስትመንት አዋጭነት ጥናት የሚሰሩና የአቅም ግንባታ ስራዎችን የሚያከናውኑ የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች የዚሁ ማሳያዎች ናቸው። እነዚህ ተግባራት ኢንስቲትዩቱ የፈፃሚ አካላትን አቅም እንደሚገነባ አመላካቾች ስለመሆናቸው ዋና ዳይሬክተሩ ይገልፃሉ።

እንደዶክተር ማንደፍሮ ገለፃ፣ በእሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ተዋንያንን ማቀናጀት ሌላው የኢንስቲትዩቱ ተልዕኮ ነው። በዚህ የኢንስቲትዩቱ ዓላማ ረገድ ከሚጠቀሱ ተግባራት መካከል አንዱ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ከአርሶ አደሩ ጋር ማስተሳሰር ነው። ለምሳሌ ያህል በኩታ ገጠም እርሻ የብቅል ገብስ የሚያመርቱ አርሶ አደሮችን ከብቅል አምራች ፋብሪካዎች ጋር እንዲሁም የዘይት ግብዓቶችን የሚያመርቱ አርሶ አደሮችን ከዘይት አምራች ፋብሪካዎች ጋር ማገናኘት የዚህ ማሳያዎች ናቸው።

ኢንስቲትዩቱ ካከናወናቸው ውጤታማ የግብርና ሽግግር ተግባራት መካከል አንዱ የኩታ ገጠም እርሻ ዘዴ (Agricultural Commercialization Clusters/ Cluster Farming) ነው። ዶክተር ማንደፍሮ ኢንስቲትዩቱ ይህን የአስተራረስ ዘዴ ተግባራዊ ያደረገበትን አሰራር አስመልክተው ሲያስረዱ ‹‹ትራንስፎርሜሽን ማለት ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ አስተራረስ ተላቆ ምርትን ለገበያ ወደማቅረብ መሸጋገር ነው። አንድ አካባቢ ለኩታ ገጠም እርሻ ከተለየ በኋላ ስልጠና ይሰጣል፤ከዚያም ድንበር አልባ ሆኖ ይታረስና አርሶ አደሮቹ ባለድርሻ ይሆናሉ። እርሻው በትራክተር፣ የአረም ርጭት፣ በአውሮፕላንና በሌሎች መሳሪያዎች እንዲሁም አጨዳም በኮምባይነር ይከናወናል። ይህ ሲሆን አርሶ አደሮቹ ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ እርሻ ወደ ኢንተርፕራይዝነት አድገው ከሀገር ውስጥ ገበያ አልፈው ለውጭ ገበያ ወደማቅረብ ይሸጋገራሉ። በ10 የሰብል ዓይነቶች (ስንዴ፣ ጤፍ፣ በቆሎ፣ ገብስ፣ ሰሊጥ፣ አቮካዶ፣ ሙዝ፣ ማንጎ፣ ቲማቲምና ሽንኩርት) የተጀመረው ይህ አሰራር እስካሁን በ300 ወረዳዎች ተግባራዊ ተደርጓል›› ይላሉ።

የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ይፍሩ ታፈሰ በበኩላቸው፣ ኤጀንሲው ካከናወናቸው ተግባራት መካከል በአፈር ለምነትና በግብርና ሜካናይዜሽን ላይ የተሰሩ ስራዎችን በማሳያነት ይጠቅሳሉ። ‹‹የአፈር ለምነት መጎዳት ከግብርናው ዘርፍ ችግሮች መካከል አንዱ ነው። ከ800 ወረዳዎች በተሰበሰበ 80ሺ የአፈር ናሙና ላይ ጥናት በማድረግ አካባቢዎቹ ምን ዓይነት ማዳበሪያዎች እንደሚያስፈልጋቸው በመለየት ምርታማነት እንዲጨምር ያስቻሉ ስራዎች ተከናውነዋል። ግብርናውን በሜካናይዜሽን አሰራር ለመደገፍ ሲሰራበት የነበረው አሰራር ብዙ ችግሮች ነበሩበት። የግብርና ሜካናይዜሽን ስራዎችን የሚያሳልጡ ግብዓቶች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡት በቀረጥ ነበር። ቀረጥ ተከፍሎባቸው ሲገቡ ለአርሶ አደሩ የሚቀርቡበት ዋጋ ውድ እንደሚሆን በጥናት የተደገፈ ምክረ ሃሳብ ለመንግሥት አቅርበን ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ ማድረግ ተችሏል። ይህም ግብዓቶቹ በቀረጥ ሲገቡ ከሚከፈልባቸው ዋጋ ባነሰ ገንዘብ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ እንዲሆኑ እድል ፈጥሯል። ይህን ለመደገፍም የሜካናይዜሽን አገልግሎት ማዕከላት (Mechanization Service Centers) ተቋቁመዋል›› ይላሉ።

‹‹ኤጀንሲው የተቋቋመው በግብርናው ዘርፍ ውስጥ ያሉ ተቋማትን አቅም በመገንባትና የተሻሻለ አሰራር እንዲተገበሩ በማገዝ የግብርና ሽግግርን እቅድን ለማሳካት ነው›› የሚሉት ዶክተር ይፍሩ፣ ኢንስቲትዩቱ ከምርምር ጀምሮ እስከ ገበያ ድረስ የሚዘልቅ የአሰራር ሰንሰለት እንዳለውም ያስረዳሉ። ‹‹በዚህ ሰንሰለት ውስጥ አንዱ ደረጃ ችግር ካጋጠመው ከእቅዱ የሚጠበቀውን አጠቃላይ ውጤት ስለሚያበላሸው ስራዎቻችንን የምንሰራው በቅንጅት ነው። ኢንስቲትዩቱ በግብርና መዋቅሮችና አደረጃጀቶች በኩል ከአርሶ አደሩ ጋር የቅርብ ግንኙነት አለው። እነዚህን መዋቅሮች በመጠቀም ለአርሶ አደሮች ስልጠና የመስጠትና የመከታተል ስራዎችን እንሰራለን። እኛ የጀመርነው ኩታ ገጠም የአስተራረስ ዘዴ ተስፋፍቶ ዛሬ ያለበት የተሻለ ደረጃ ላይ ደርሷል›› ይላሉ።

በግብርና ሚኒስቴር ስር ካሉ ተቋማት መካከል አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ አደረጃጀቱ ኢንስቲትዩት ሆኖ ከተዋቀረ በኋላ ከአስፈፃሚውም ሆነ ከአጋር አካላት ጋር በሚኖረው የሥራ ግንኙነት ለውጥ ላይ ለውጥ ይጠበቃል። አቶ ኡመር በግብርና ሚኒስቴርና በኢንስቲትዩቱ መካከል ስለነበረውና በቀጣይ ስለሚኖረው የስራ ግንኙነት ሲያስረዱ ‹‹ከዚህ ቀደም ከኢንስቲትዩቱ ጋር የምንሰራው፣ ጥናት አጥንቶ ሌላ ፈፃሚ አካል በመጠበቅ ነበር። አሁን ግን ኢንስቲትዩቱ ያደረገው ጥናት ከሚኒስቴሩ ጋር በትብብር ይፈፅማል። እንደተጠሪ ተቋም እቅድ ወይም ሪፖርት መቀበል ሳይሆን ስራዎቹን በጋራ እንፈፅማለን። በእርግጥ ከሌሎች ተጠሪ ተቋማት ጋር ያለን ግንኙነት የአለቃና የምንዝር ሳይሆን ውጤትን መሰረት ያደረገና ያቀድነውን ከግብ የሚያደርስ ነው›› ብለዋል። ኢንስቲትዩቱ በእውቀት የተደገፈ ቁርጠኛነት ያላቸው ባለሙያዎች እንዳሉት ጠቁመው፣ የግብርናውን ዘርፍ ችግሮች የመለየት ኃላፊነቱን ይበልጥ ለማሳደግ ወደፊት የሚያከናውናቸው ተጨማሪ ተግባራት እንደሚኖሩ በመገንዘብ ጥረቱን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባው አሳስበዋል።

‹‹ከአጠቃላይ ሀገራዊ ፍላጎቱ አንፃር ገና ብዙ መስራት ይገባል። በሰብልና ሆርቲካልቸር ዘርፎች ላይ የነበረውን ትኩረት ወደ እንስሳት ሀብት ዘርፍም ማስፋት ያስፈልጋል። በግብርናው ዘርፍ ያለው ሀገራዊ ፍላጎት እያደገ ስለሆነ ኢንስቲትዩቱ ለዚህ ፍላጎት የሚመጥን ምላሽ መስጠትን ታሳቢ ያደረገ ቁመና ሊኖረው ይገባል›› ብለዋል።

ዶክተር ይፍሩም ኢንስቲትዩቱ ከግብርና ዘርፍ አካላት ጋር ያለው ትብብር ጠንካራ እንደሆነ ያስረዳሉ። ‹‹ከግብርና ሚኒስቴር ጋር ያለን ትብብር ከምንጊዜውም በላይ የተቀናጀ ነው። ለአብነት ያህል የመንግሥት የአስር ዓመት የልማት እቅድ ሲዘጋጅ አብረን አዘጋጅተናል። የግብርናው ዘርፍ ሊለወጥ የሚችለው ምን ብናደርግ ነው ለሚለው ወሳኝ ጉዳይ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ለይተናል። ግብርናውን ማዘመን፣ መስኖን ማስፋፋት፣ ግብርናውን ከአምራቹ ዘርፍ ጋር ማስተሳሰር እንዲሁም የግብርና ኢንቨስትመንትን ማሳደግ ትኩረት የሚሹ ቁልፍ ጉዳዮች ናቸው›› በማለት ይገልፃሉ።

ተቋሙ ወደ ኢንስቲትዩትነት ከተሸጋገረ በኋላ የምርምር ስራዎችን እንዲያከናውን ተጨማሪ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። ዶክተር ማንደፍሮ እንደሚሉት፣ ኢንስቲትዩቱ በቀጣይ የሚያከናውናቸው የምርምር ተግባራት የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሚያከናውናቸው የሰብል እንስሳት ምርምሮችን ሳይሆን ስርዓት ተኮር የሆኑ የምርምር ስራዎችን ነው። የግብርናው ዘርፍ ምርምር ስለሚሻሻልበት መንገድም ምርምር ማድረግ ያስፈልጋል። የኤክስቴንሽን፣ የግብይትና የኢንዱስትሪ ትስስር ስርዓቶች የበለጠ ውጤታማ የሚሆኑባቸውን መንገዶችን የሚጠቁሙ ምርምሮች ይደረጋሉ። ከሰብል በተጨማሪ በእንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች፣ በተለይም በዶሮ እና ወተት፣ ላይ አተኩሮ እንደሚሰራም ተናግረዋል።

ዶክተር ማንደፍሮ ለኢንስቲትዩቱ ዓላማ መሳካት ድጋፍ የሚያደርጉ በርካታ ሀገራትና ተቋማት እንዳሉ ጠቁመው፣ በቀጣይ ስራዎቻችን አርሶ አደሮቹ ምርታማነታቸውን አሳድገው ወደ ትልልቅ አምራችነት እንዲሸጋገሩ ጥረታችንን እንቀጥላለን። የግብርናው ሽግግር እንዳይሳካ መሰናክል የሚሆኑትን ነገሮችና መፍትሄዎቻቸውን እንለያለን። በጥናት የተገኙት ሃሳቦች እንዲተገበሩ እናደርጋለን›› ብለዋል።

**ኢንስቲትዩቱ ባለፉት ዓመታት በግብርናው ዘርፍ ያሉ ክፍተቶችን በመለየትና ምርታማነትን በማሳደግ ረገድ ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል። በፖሊሲና በአሰራሮች ውስጥ ያሉ ችግሮችን የመለየትና መፍትሄ የመጠቆም ተግባራትን አከናውኗል። ለአብነት ያህል በአሁኑ ወቅት እስከ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት የመሸፈን አቅም መፍጠር በተቻለበትና በርካታ አርሶ አደሮችን ባሳተፈው የኩታ ገጠም እርሻ ዘርፍ ተጨባጭ ለውጥ መፍጠር ችሏል፤ የኩታ ገጠም የአስተራረስ ዘዴን ተግባራዊ ያደረጉ አርሶ አደሮችን የምርታማነት ችግሮች ሊፈታ የሚችል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጓል።**

ማህበራዊ

# አስኳላ

# መምህራንንና ተማሪዎችን ተጠቃሚ ያደረገ ስልጠና

**አስናቀ ፀጋዬ**

የምስራቅ አፍሪካ በይነ መንግስታት ድርጅት /ኢጋድ/ ከአንድ አመት በፊት  የጀመረው  የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ስልጠና አንዱና ወሳኙ የጅቡቲ ድንጋጌ አካል ሲሆን ስደተኞች፣ ከስደት ተመላሾች እና ስደት አስተናጋጅ ማህበረሰቦች ትምህርት እቅድ ጋር አብሮ የሚሄድ መርሃግብር ነው።

መርሃግብሩም ስደተኞች፣ ከስደት ተመላሾችና ስደት አስተናጋጅ ማህበረሰቦች በከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች ተደራሽነታቸውን ማጠናከር ላይ ያተኩራል። መርሃ ግብሩ ከተጀመረበት እ.ኤ.አ ከየካቲት 2021 እስከ ግንቦት 2022 ድረስ  በሙከራ ደረጃ ኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ኡጋንዳ ተሳትፈውበታል።

የመምህራን ስልጠና መርሃግብሩ የሙከራ ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ማድረግ የጀመረው በሶስቱ ሀገራት የሚገኙ ሁለት ክልሎችን በመምረጥ ሲሆን እነዚህም በኢትዮጵያ ጋምቤላና ሶማሊያ፣ በሱዳን ነጭ አባይና ገዳሪፍ /ከከሰላ ጋር በማቀናጀት/ እንዲሁም በኡጋንዳ ደቡብ ኡጋንዳና ደቡብ ናይል ናቸው። የአስር ቀን የመምህራን ፍላጎት ዳሰሳ ከተሰራና አስፈላጊው ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ መምህራን ተመርጠው ስልጠና እንዲወስዱ ተደርጎ መርሃ ግብሩ እ.ኤ.አ እስከ ግንቦት 2022 ድረስ በሶስቱ ሀገራት ሲከናወን ቆይቷል።

መርሃ ግብሩ ከተጀመረ ወዲህ እ.ኤ.አ እስከ ግንቦት መጨረሻ ድረስ ከሶስቱ ሀገራት 600 መምህራን ሥልጠና ወስደው ስደተኞችን፣ ከስደት ተመላሾችንና ስደት አስተናጋጅ ማህበረሰቦችን እያስተማሩ ይገኛሉ። ይህም በመጀመሪያውና በሁለተኛው ዙር የሰለጠኑ 200 መምህራንን ያጠቃልላል።

ከነዚህ ውስጥ 106 ያህሉ በመጀመሪው ዙር እንዲሁም 100ዎቹ በሁለተኛው ዙር በጥቅሉ 206ቱ ከኢትዮጵያ ናቸው።  በመጀመሪያው ዙር ከሰለጠኑ 106 ኢትዮጵውያን መምህራን መካከል ደግሞ 89 ወንዶች፤ 17 ደግሞ ሴቶች እንዲሁም በሁለተኛው ዙር ኢትዮጵያውያን ሰልጣኞች 90 ወንዶች 10 ሴቶች ናቸው።

ኢትዮጵያዊቷ መምህርት ትግስት ወልደሃና የዚህ ስልጠና ተጣቃሚ ከሆኑት ውስጥ አንዷ ስትሆን በሶማሌ ክልል ዶሎ አዶ የስደተኞች መጠለያ ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ ባዮሎጂ ትምህርት ታስተምራለች። በመምህርነት ሙያም መስራት ከጀመረች ስድስት አመት ሆኗታል።  በዚህ የስደተኞች ካምፕ ውስጥ ማስተማር ከጀመረች ደግሞ ሶስት አመታትን አስቆጥራለች።

መምህርት ትግስት ወደዚህ የስደተኞች ካምፕ ለማስተማር ከመምጣቷ በፊት በሶማሌ ክልል ዶሎ አዶ ከተማ ለአራት ተከታታይ ዙር የኢጋድ መምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ተከታትላለች።  በስልጠናውም የመማር ማስተማር ሂደቱን የሚያግዙ የትምህርት ማበልፀጊያ፣ ስነልቦናና ማህበራዊ ድጋፍ፣  የህይወት ክህሎትና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (አይ ሲ ቲ) ኮርሶችን ወስዳለች።

ስልጠናውን ካጠናቀቀች በኋላ እንደ ኢጋድ አባል ሀገር በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል በሚገኘው የዶሎ አዶ የስድተኞች መጠለያ የባዮሎጂ ትምህርት እያስተማረች ትገኛለች።  በኢጋድና በጂ ቲ ዜድ ትብብር ያገኘችው ስልጠና የመምህርነት ሙያዋን ለማበልፀግ እንደረዳትና ራሷንም ለማብቃት እንዳስቻላት ትናገራለች።  እንዲህ አይነቱ ስልጠና ተጓዳኝ ድጋፍ መሆኑንና ሞራል የሚሰጥና የሚያበረታታ እንደሆነም መምህርት ትግስት ትገልፃለች።

ስልጠናው ትምህረቱን በተረጋጋ መንፈስ ለማስኬድ እንደረዳት ገልፃ፤ በስደት ጣቢያው ያሉ ተማሪዎችን ሊደግፍ የሚችሉ በርከታ ጠቃሚ ነገሮችን ከስልጠናው አግኝታ ስታስተምር እንደቆየችም ትጠቁማለች።

የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ትምህርት የኢትዮጵያ አስተባባሪ አቶ ከፍያለው አያኖ እንደሚናገሩት የኢጋድ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ስልጠና መርሃ ግብር ከመጀመሩ በፊት ትምህርቱን ለማስኬድ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች  ተዘጋጅተዋል። ስልጠናው ደግሞ በመምህራን የስልጠና ፍላጎት ላይ



**የኢጋድ አባል ሀገራት መምህራን፣ አሰልጣኞችና አስተባባሪዎች የልምድ ልውውጥ አድርገዋል፤**

ያተኮረ  ነበር።  ስልጠናውን ለመስጠት የተፈለገበት ዋነኛ አላማም በስደተኞች፣ ከስደት ተመላሾችና ስደት አስተናጋጅ ማህበረሰብ ተማሪዎች ላይ የትምህርት ጥራት ለውጥ ለማምጣት ነው።

ስደተኞች፣ ከስደት ተመላሾችና ስደት አስተናጋጅ ማህበረሰብ ተማሪዎች በአብዛኛው ዩኒቨርሲቲ እንደማይገቡ በመረዳትም ነው በኢጋድ አነሳሽነት ስልጠናው የተጀመረው።

በዚህ ዓላማ መነሻ መምህራን በትምህርት ማበልፀጊያ፣ ስነልቦናና ማህበራዊ ድጋፍ፣ የህይወት ክህሎትና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (በአይ ሲ ቲ) ላይ በሁለት ዙር ስልጠናዎችን ወስደው አጠናቀዋል። ከኢትዮጵያም 206 የሚሆኑ በጋምቤላና በዶሎ አዶ የስደተኞች ጣቢያ ለሚያስተምሩ የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ይኸው ስልጠና በሁለት ዙር ተሰጥቷቸው ካጠናቀቁ በኋላ እያስተማሩ ይገኛሉ።

በዚህ የሁለት ዙር ስልጠና የሰለጠኑት 206 የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ከ10 ሺ በላይ ለሚሆኑ በጋምቤላና በዶሎ አዶ የስደተኞች ጣቢያ ለሚገኙ ስደተኞች፣ከስደት ተመላሾችና ስደት ተቀባዮች የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ተደራሽ ይሆናሉ። በዚህም ተማሪዎቹ በተዘዋዋሪ የዚህ ስልጠና ተጠቃሚ ይሆናሉ።

አስተባባሪው እንደሚሉት የትምህርት ጥራት እንዲህ በቀላሉ በአንድ ግዜ የሚመጣ ባለመሆኑ ለትምህርት ጥራት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ በርካታ ነገሮች በመኖራቸውና ከነዚህ ውስጥም ካሪኩለም፣ የመምህራን ስልጠና፣ የተማሪዎች ዝግጅት፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች ሌሎችም ግብዓቶች  ላይ መስራት ያስፈልጋል።   በተለይ ደግሞ ለትምህርት ጥራት መረጋገጥ ዋነኛው መምህራን በመሆናቸው መምህራን ላይ አተኩሮ መስራት ውጤታማ ያደርጋል ።

መምህራን ተማሪዎችን በአግባቡ ካላስተማሩ ውጤታቸው ሊሻሻል አይችልም።   የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ዋናውና የመጀመሪያው እቅድም በመምህራን ላይ ለመስራት ነው። በዚህም እስካሁን ድረስ በስልጠናው አማካኝነት ጥሩ ውጤት ማምጣት ተችሏል።  የተማሪዎች ውጤትም ከአምናው ጋር ሲወዳደር መሻሻል አሳይቷል።

መምህራን ተማሪዎችን እንዴት ተቀብለው ማስተማር እንዳለባቸውም በስልጠናው ለማወቅ ችለዋል።  ከተማሪዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነትም አጠንክሯል።  መምህራን የተሻሉ የማስተማር ስነ ዘዴዎችንም እንዲከተሉ አድርጓቸዋል።  ይህም በተማሪዎች ውጤት መሻሻል ላይ የራሱን አስተዋፅኦ አበርክቷል።

የትምህርት ጥራት የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ሀገራት ችግር ቢሆንም በመጠንና በስፋት ግን ይለያያል ። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የትምህርት ጥራት ችግር ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። ይህም ቢሆን ግን በአንድ ጀምበር ለውጥ ይመጣል ብሎ ማሰብም ከባድ ነው ።  በኢጋድ አነሳሽነት

**የትምህርት ጥራት የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ሀገራት ችግር ቢሆንም በመጠንና በስፋት ግን ይለያያል ።  በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው  የትምህርት ጥራት ችግር ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል**

ለመምህራን የተሰጠው ስልጠና እንደመነሻ ሆኖ ቀስ በቀስ ግን ሌሎች ስራዎችን በማከል የትምህርት ጥራቱ በሚፈለገው ደረጃ እንዲደርስ ማድረግ ይቻላል።

ስምንቱ የኢጋድ አባል ሀገራት ኢትዮጵያ፣ ኡጋንዳ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ሱዳን፣ ኤርትራ፣ ሶማሊያ፣ ኬንያና ጅቡቲ ሲሆኑ የመምህራን ስልጣና ፕሮግራሙ በሙከራ ደረጃ በኢትዮጵያ፣ ኡጋንዳና ሱዳን ነው የተጀመረው። በቀጣይም ወደሌሎቹም የኢጋድ አባል ሀገራት እየሰፋ እንደሚሄድ የተገለጸ ሲሆን በተለይ ስልጠናውን በጅቡቲና ኬንያ ለመጀመር ውጥን ተይዟል።

የኢጋድ የትምህርት፣ሳይንስ ቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን ከፍተኛ አስተባባሪ ዶክተር ከበደ ካሳ በበኩላቸው እንደሚሉት ስልጠናው የተጀመረው በሶስት የኢጋድ አባል ሀገራት ማለትም ኢትዮጵያ፣ ሱዳንና ኡጋንዳ ነው።  በመምህራን ስልጠና ላይ ማተኮር የተፈለገበት ዋነኛ ምክንያትም የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የመምህራን የሙያ ጥራትና ተነሳሽነት ወሳኝ በመሆኑ ነው።  የመምህራንን አቅም መገንባት ካልተቻለ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣትም አስቸጋሪ ይሆናል ።

አባል ሀገራት በትምህርት ላይ ከሚያደርጉት አስተዋፅኦ በተጨማሪ ኢጋድም ትምህርትን እንደ አህጉራዊ መተሳሰሪያ አድርጎ ስለሚሰራ  በመምህራን ላይ የሚሰራው ስራ ታች ተማሪዎች፣ ቤተሰቦቻቸውና ህብረተሰቡ ላይ ጥሩ ውጤት ሊያመጣ ይችላል በሚል የስልጠና ፕሮግራሙን ጀምሯል።

ይህን በሙከራ ደረጃ የተጀመረውን ሥልጠና በመያዝ በሌሎች አባል ሀገራት ያሉ በርካታ መምህራንን ሊያሳትፍ በሚችል መልኩ ለመስራት ታስቧል።  ለዚህም የልምድ መለዋወጫ ስብሰባዎችን (ወርክሾፖችን) በአዲስ አበባ ተዘጋጅቶ የተሰሩ ስራዎች ተገምግመዋል።   በጎ ተሞክሮዎችም ተጋርተዋል። ያጋጠሙ ችግሮችም ተለይተዋል።   ለሚቀጥለው ርምጃ መነሻ ግብአቶችም ተሰብስበዋል።

እስካሁን ባለው ሂደትም የተሰሩ ስራዎች በጥሩ ሁኔታ ተጠናቀዋል።  በተለይ ስልጠናው የተካሄደባቸው ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች የሚገኙባቸው ሀገሮችም ከፍተኛ ትብብር አድርገዋል። ይህንኑ ትብብር በሌሎች የኢጋድ አባል ሀገራት ለማሳደግና ወደፊት ከዚህ የተሻለ ስራ ለማከናወን የሚያስችል ግንዛቤ ለመጨበጥ ተችሏል።

ለመምህራን በተሰጠው ስልጠና መነሻነት የመጡ ለውጦች ወደፊት የሚለኩ ሆነው እስካሁን በሁለት ዙር በሶስቱም ሀገራት 600 መምህራን ሰልጥነዋል። ከዚህ ውስጥ 30 ከመቶ የሚሆኑት ሴት መምህራን ናቸው።  ይህም ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ያሳተፈ ስራ መሰራቱን ያሳያል ።  በስደተኞችና ከስደት ተመላሽ ጣቢያዎች የሚታየውን የትምህርት ጥራት ጉድለት በማስተካከል ረገድም ስልጠናው ትልቅ ለውጥ አምጥቷል።

በተለይ በመምህራን ተነሳሽነትና በተማሪዎች ትምህርት አቀባበል በኩል ለውጦች እየታዩ ነው።  የትምህርት ቤቶቹ ተነቃቂነትና የማስልጠኛ ተቋማቱ ፍላጎትም እየጨመረ መጥቷል።  ወደፊት ለሚታቀደውም ይህ እንደ ጥሩ ግብአት ሆኖ ያገለግላል።   እስካሁንም መልካም ተሞክሮዎች ከስልጠናው ተገኝተዋል።  በተለይ ግብአቱ የተሻለ እቅድ እንዲኖርና በቀጣይ ሰፋ ባለ መልኩ ለመተግበር ይረዳል።

ከዚህ አኳያ ይህ አበረታች ጅምር ውጤቱም ጥሩ በመሆኑ ወደፊት ቀጣይነት ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል።   በዚህም ሁሉንም በትምህርት ላይ የተሰማሩ በየሀገሩ ያሉ የጋራ አጋሮች ላይ ከፍተኛ ስራ ይሰራል።

እስካሁን በሙከራ ደረጃ የተከናወነው የስልጠና መርሃ ግብሩ በሶስት ሀገራት ሲከናወን የቆየ ቢሆንም ከዚህ የተገኘውን ጠቃሚ ግብአት በመውሰድ በቀጣይም በሌሎች የኢጋድ አባል ሀገራት የማስፋት እቅድ አለ።  በተለይ በቀሪዎች የኢጋድ አባል ሀገራት በኩል ፍላጎቱ ያለ በመሆኑ መርሃ ግብሩን ወደተቀሩት ሀገራት የማስፋትና በስልጠናው እንዲታቀፉ የማድረግ እድል ይኖራል።

# ‹‹በስተጀርባ ያለው ኃይል እየተዳከመ ከመጣ አሸባሪው ሸኔ ቦታ አይኖረውም››

*- ዶክተር ዲማ ነገዎ*



ፎቶ - ከደክመንት

በጋዜጣው ሪፖርተር

ዶክተር ዲማ ነገዎ የተወለዱት ኢሉአባቦራ ውስጥ ከጎሬ ከተማ ወደ 18 ኪሎሜትር ርቀት ላይ በምትገኘው ጉማሮ በተባለች ስፍራ ነው። የልጅነት ጊዜያቸውን ከቤተሰብ ጋር አሳልፈዋል። ቤተሰባቸው በግብርና ሙያ ላይ ኑሯቸውን ያደረጉ ናቸው። በልጅነታቸው በጣም የሚወዱት ነገር ታሪክና ተረቶችን ከአባታቸው እግር ሥር ቁጭ ብሎ መስማት ነበር ። አባታቸው ባይኖሩ እንኳን ሌሎች ትልልቅ ሰዎች ሳያጫውቷቸው አይውሉም። እሳቸውም ይህንን ጊዜ በጉጉት ይጠብቁት እንደነበር በአንድ ወቅት ከህይወት ገጻቸው ለዝግጅት ክፍላችን ከተናገሩት ላይ ስለእድገታቸው ትንሽ ለማስታወስ ያህል ወስደናል።

ዶክተር ዲማ ነገዎ፤ ከዘመናዊ ትምህርት ጋር የተዋወቁት በጎሬ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። በ1960 ዓ.ም በአገሪቱ ብቸኛ በነበረው ቀዳማዊ ኃይለስላሴ በአሁኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገቡ። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመርቀው ዓመታትን በስራ ካሳለፉ በኋላ ዳግም ወደ ትምህርት በመመለስ በሴኔጋል ዩናይትድ ኔሽን አፍሪካን ኢኒስቲቲዩት ፎር ኢኮኖሚክ ዴቨሎፕመንት ኤንድ ፕላኒግ ውስጥ ገቡ ። በዚህም ኢኮኖሚክ ፕላኒንግ አጠኑ። ሦስተኛ ዲግሪያቸውን በአሜሪካ አገር ቴኔሲ ዩኒቨርሲቲ በሶሾሎጂ ትምህርት መስክ ተመርቀዋል። በእንግሊዝ አገርም እንዲሁ በግጭትና የሠላም ግንባታ ዙሪያ የስድስት ወር ስልጠና ወስደዋል። በተመሣሣይ ጀርመንኛ ቋንቋ ተምረዋል።

በፖለቲካ ህይወታቸውም ዶክተር ዲማ በኦሮሞ ነጻነት ግንባር( ኦነግ) ውስጥ ትልቅ ስፍራ አላቸው። ወደ አውሮፓ አቅንተው ጀርመን ውስጥ የኦሮሞ ተማሪዎች ማህበርን በማጠናከር ለሦስት ወር ያህል ሰርተዋል። ወደ ሱዳን ሄደው የትጥቅ ትግሉን ተቀላቅለውም 13 ዓመታትን ለማህበራዊ ፍትህ ነጻነት ታግለዋል። የሶማሊያን መንግስት የዌስተር ሱማሌ ሊብሬሽን ፍሮንትና ሶማሊያ ሊብሬሽን ፍሮንት ድርጅቶችን መስርተዋል። በዚያም ውስጥ ብዙ ቁጥር ያላቸው ኦሮሞዎችን አደራጅተው ከእነርሱ በአስተሳሰብ አልስማማ ሲሉ መንግስቱ የሱማሊያን ጥቅም የሚጻረር ሥራ ሰርተሃል በሚል እንዳሰራቸው ከታሪካቸው ከሚጠቀሱት ምዕራፎች ጥቂቶቹ ናቸው።

በዛሬው ዕትማችን የሀገሪቱን ወቅታዊ ጉዳዮች አስመልክቶ ሙያዊ ሐሳብ እንዲያካፍሉን እንግዳ አድርገናቸዋል። በተለይም ደግሞ የኢትዮጵያ አሁናዊ የፖለቲካ ሥሪት እና ፈተናዎቿ፣ መፍትሄ እና መከናወን ስለሚገባቸው ሁኔታዎች እንዲሁም ‹‹አሸባሪው ሸኔ›› እየሄደበት ያለውን የጥፋት መንገድ ለመቃኘት ተሞክሯል። ከዚህም በተጨማሪ የወያኔ የግፍ አገዛዝ ዘመንና ገፅታ እና አሁናዊ ቁመናም በቃለ ምልልሱ አካተናል ።

**አዲስ ዘመን፡- የለውጡ ኃይል ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ በሀገሪቱ የመጣውን የፖለቲካ ሂደት እንዴት ይመለከቱታል፤ ለውጡ ለኦሮሞ ህዝብስ ምን ይዞ መጣ ?**

**ዶክተር ዲማ ነገዎ፡-** ይህ ከባድ ጥያቄ ነው። በእርግጥ ይህ ለውጥ እንዲመጣ የኦሮሞ ህዝብ ታግሏል። በተለይ ወጣቱ ከፍተኛ መሥዕዋትነት ከፍሏል። ይህ ለውጥ እንዲመጣ በማድረግ ውስጥ ሚናው ከፍተኛ ነው። ሁለተኛ ለውጡም እንዲመጣ ያደረገው ለሀያ ሰባት ዓመታት በኦሮሞ ህዝብና በሌላው ህዝብ ላይ ተንሰራፍቶ የቆየው የወያኔ የጭቆና አገዛዝ ነው። ይህን የጭቆና አገዛዝ መሸከም ስላቃተው መጨረሻ ላይ የህዝብ ኃይልና ቁጣ ገንፍሎ ወጥቶ በጥቂት ጊዜ ውስጥ ነው ለውጥ የመጣው። ሦስት ዓመት ነው የፈጀው ከዚያም በፊት ትግሉ ሲብላላ ነው የቆየው ፤ ከዚያው አሸንቅጥሮ ጣለው።

ወያኔም ለውድቀቱ ስላልተዘጋጀና ውድቀቱን መቀበል ስላቃተው በሌላ መንገድ ተመልሶ ስልጣኑን ለመቆጣጠር ሞከረ። በተለይ ባለፉት የለውጥ ዓመታት

**የወያኔ ፕሮግራም ከዱሮ ጀምሮ ይታወቃል። አንድም ብሄር አንድ እንዲሆን አይፈለግም። በተለይ አማራ እና ኦሮሞ አንድ እንዳይሆን በደንብ ሰርተዋል፤ በዚህም መቀጠል ይፈልጋሉ። ይህ በተወሰነ ደረጃ አሻሽለው ለመቀጠል ሰርተዋል። ኦሮሞ እና አማራ፣ ሱማሌ እና አማራ፣ ሱማሌ እና አፋር ለማጋጨት ብዙ ሠርተዋል። በተወሰነ ቦታ ተጠቅመውበታል።**


እየታየ ያለው ሁኔታ በአንድ በኩል ለውጡን በማስቀጠል በሚፈልጉ ሃይሎች እና ለውጡን ቀልብሶ ወደ ዱሮው ቦታ ለመመለስ በሚፈልጉ ሃይሎች መካከል እየተደረገ ያለ ትንቅንቅ ነው። ይህ ትንቅንቅ እስከ ጦር መማዘዝ እና የብዙ ኢትዮጵውያን ህይወት የቀጠፈ፣ ብዙ ንብረት እንዲወድም ያደረገ እና ከፍተኛ ንብረትን የህዝብ ሃብት የጠፋበትና በሚሊዮኖች ዜጎች የተፈናቀሉበት መሆኑን ያየንበት ነው። እናም ከፍተኛ የሆነ እና በለውጡም ብዙ ውጤቶች ተገኝተዋል።

ቀድሞ በነበረው የወያኔ ስርዓት ከአራት ዓመት በፊት የነበረውና ዛሬ ያለው የተለየ ነው። ያስገኘው ጥቅም አለ። እንዲያውም ሆኖ ደግሞ ይህ ትንቅንቅ ባይኖር ኖሮ ከአሁኑ የተሻለ ለውጥ ይመጣ ነበር። የኢኮኖሚ እና ሌሎች ለውጦችም ይታይ ነበር። ነገር ግን ለውጡን ለመቀልበስ በሚደረገው ጥረት ምጣኔ ሃብቱን ጎድቷል፤ በተለይ የታችኛው የማህበረሰብ ክፍል ኑሮ ተመሰቃቅሏል፤ በሀገር ውስጥ የምናየው የኑሮ ውድነት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የውጭ ጫናዎች ሁኔታዎች ቢኖሩም በዋናነት የዚህ ትንቅንቅ ውጤት ናቸው። ታሪክ ወደኋላ አይሄድም፤ ለውጡ ይቀጥላል፤ ግን እክሎች አጋጥመውታል ፤ አሁንም ሊያጋጥሙት ይችላል ይህን መገመት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- አሸባሪው ሸኔ በምዕራብ ወለጋ ዞን በንጹሃን ላይ የሚፈፅመውን ጭፍጨፋ እንዴት ይመለከቱታል?**

**ዶክተር ዲማ ፡-** ወለጋ ውስጥ እንዳልኩት ከአራት ዓመት በፊትም ህዝብ ሲጨፈጨፍ ነበር። ይህ አዲስ ነገር አይደለም። ነገር ግን ማንም ቢሆን በማንም ላይ ይህ ድርጊት መፈፀም የለበትም ብዬ አምናለሁ። የብዙ ንፁሃን ዜጎች ደም ሲፈስ ነበር። ወደ ኋላ ከሄድን ረጅም ነው። 100 ዓመት ኢትዮጵያ ውስጥ ጦርነት ነበር፤ ልማት አላካሄድንም። በተለይ ደግሞ ንጹሃን የፖለቲካ ግጭት ውስጥ ምንም ሚና የሌላቸው ህዝቦች፣ ዜጎች እዚህ ውስጥ መማገድ የለባቸውም። ማንም ድርጅት የፖለቲካ ዓላማ

# ወቅታዊ



ካለው በሰው ፍጡር ላይ ወንጀል መፈፀም የለበትም። የፖለቲካ ዓላማ አለኝ፤ ህዝባዊ ዓላማ አለኝ የሚል በማንም ላይ ይህ መሰል ድርጊት መፈፀም የለበትም።

በእኔ አረዳድ በኢትዮጵያ ውስጥ በብሄሮች አለመግባባት አለ የሚል እምነት የለኝም። ያለው የፖለቲካ አለመግባባት ነው። የሚስተዋለው ግጭትም የፖለቲካ ግጭት ነው። በአፍሪካ ውስጥ ግጭቱን የጎሳ ግጭት የሚያደርጉት የውጭዎቹ ናቸው። ዱሮ ሊሆን ይችላል። አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ፖለቲካ ውስጥ አለመግባባትና አለመጣጣም አለ። ግማሹ በብሄር፤ ግማሹ በሃይማኖት፣ ግማሹ በተወለደበት አካባቢ ለመደራጀት ይሞክራል። ማንነት ደግሞ በቀላሉ ሰዎችን ለማንቀሳቀስ ስለሚቀል ይጠቀሙበታል። አንዳንድ አካላት ግጭቶችን የሚያራግቡት በዚህ ውስጥ ድጋፍ ለማሰባሰብ ነው።

የወያኔ ፕሮግራም ከዱሮ ጀምሮ ይታወቃል። አንድም ብሄር አንድ እንዲሆን አይፈለግም። በተለይ አማራ እና ኦሮሞ አንድ እንዳይሆን በደንብ ሰርተዋል፤ በዚህም መቀጠል ይፈልጋሉ። ይህ በተወሰነ ደረጃ አሻሽለው ለመቀጠል ሰርተዋል። ኦሮሞ እና አማራ፣ ሱማሌ እና አማራ፣ ሱማሌ እና አፋር ለማጋጨት ብዙ ሠርተዋል። በተወሰነ ቦታ ተጠቅመውበታል። ከአራት ዓመት በፊት በነበረው ግጭት ከሱማሌ እና ኦሮሚያ አዋሳኝ አካባቢ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ተፈናቅለዋል። አሁንም ወያኔ ይህን ለማስቀጠል ነው የሚሰራው ። በዚህ ሁሉ ውስጥ የመጨረሻ ውጤት ገፈት ቀማሽ ግን የትግራይ ህዝብ ነው። ለወያኔ ስልጣን ብለው መሳሪያ እየሆኑ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በኦሮሞ ፖለቲካ ውስጥ ዘመናትን እንዳሳለፈ ሰው በአሁኑ ወቅት በክልሉ ውስጥ እየተካሄደ ያለውን ሁኔታ እንዴት ይመለከቱታል፤ በክልሉ ሠላምን እንዴት ማስፈን ይቻላል ብለው ያምናሉ ?**

**ዶክተር ዲማ ፡-** በኦሮሚያ ክልል የሚታየው ሁኔታ አስቸጋሪ ነው። ሠላም ከደፈረሰ ሰነባብቷል። በወቅቱ መፍትሄ ቢፈለግ ይህን ያክል ችግር አይፈጥርም ነበር። አሁን እየተስፋፋ ነው፡ ወደ መሃል ሀገርም ተንሰራፍቷል። ይህ ሁኔታ እንደማስበው በሌላ ቦታ ካለው ችግር ጋርም ይያያዛል። ብዙ ሰው ኦሮሚያ ውስጥ ያለውን ችግር ለብቻ ለይተው ያያሉ። ይህን የኦሮሞ ነፃነት ግንባር አደረገው በሚል ነው የሚወራው። በእርግጥ ኦነግ በኦሮሞ ህዝብ የሚወደድ ድርጅት ነው። ለህዝቡ መብት ታግሏል። ነገር ግን አሁን የሚታየውና ዱሮ የነበረው ለየቅል ነው።

ወያኔ ለ27 አመታት ስልጣን ላይ በቆየበት ወቅት ዋነኛ የትኩረት ቦታው እና አቅጣጫው የነበረው ኦሮሚያ ክልል ነው። ኦሮሚያን መቀማት ላይ ነው ያተኮረው። ስልጣን ከመያዛቸው በፊት የኦሮሞ ሀቀኛ ሃይል እያለ እውነተኛ ታጋዮችን በማግለል የሚፈልጉትን ስራ ሲሰሩ ነበር። ይሁንና የኦሮሞን ህዝብ እንቅስቃሴ መግታት አልቻሉም። በመጨረሻም ህዝብ አስወግዶታል። በሺዎች መሥዋዕት ከፍለው ነው ለዚህ መብቃት የተቻለው። የኦሮሞ ታማኝ ድርጅቶች ውስጥ በመግባት የራሳቸውን ሴራ በመሸረብ ዓላማቸውን ለማሳካት ጥረዋል። ለኦሮሞ እውነተኛ ተቆርቋሪዎችን በማግለል የራሳቸውን ፍላጎት ለማሳካት የሚያግዙትን አካላት በዘዴ አስቀምጠዋል።

በአሁኑ ወቅት በኦሮሞ ነፃነት ግንባር ሥም የሚንቀሳቀሱት የወያኔ ተላላኪ ናቸው ። ትክክለኛ የኦሮሞ ወዳጅ ያልሆኑ ናቸው። ይሁንና ለኦሮሞ ህዝብና ነፃነት የሚታገሉ የሉም ማለት አይደለም፡ ከበስተጀርባ ያለውን ሚስጥር አልተረዱትም። ኦሮሚያ ማለት ኢትዮጵያ ማለት ነው። ኦሮሚያ ተበጠበጠች ማለት መላ ኢትዮጵያ ተበጠበጠች ማለት ነው። የሀገሪቱ ትልቁ ሃብት በኦሮሚያ ውስጥ ነው። ኦሮሚያ ማዕከል ናት።

ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትልካቸውና የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙት አብዛኛው መገኛው ኦሮሚያ ነው። በመሆኑም ኦሮሚያን መበጥበጥ ማለት መንግስትን ማዳከም ነው፤ ይህም የወያኔ ስትራቴጂ ነው። በጦርነቱ ማሸነፍ ባለማቻላቸው በተለያየ ቦታ ግጭት በመቀስቀስ ማትረፍ ይፈልጋሉ። በዚህ ብቻ ሳይሆን በአማራ፣ በጋምቤላ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል እና ሌሎች አካባቢዎች የሚስተዋሉ ችግሮች የወያኔ ጥንስስ ናቸው። ወያኔ ላለፉት 27 ዓመታት በርካታ የሚመቿትን ነገሮችን ለራሷ ስትሰራ ነበር።

አሁን እነዚህን አካላት በመከፋፈልና በማነሳሳት እየተጠቀሙ ነው። ይህን አውቀው አብረው የሚሰሩ አሉ። ሳያውቁ የእነዚህን አካላት መሳሪያ እና መጠቀሚያ የሆኑ አሉ። አውቀው የኦሮሞን ህዝብ መብት እናስከብራለን ብለው የሚታገሉ አሉ። ያልተመለሱ የኦሮሞ ህዝብ ጥያቄዎች አሉ። ለምሳሌ ከወረዳ ጀምሮ እስከ ላይኛው የመንግስት እርከን የመልካም አስተዳደር መስፈን አለበት። በአሁኑ ወቅት በብዙ የመንግስት መዋቅር ውስጥ ያሉት በወያኔ የአገዛዝ ዘመን የነበሩት ናቸው። ተለውጠው ከሆነ መልካም ነው። ግን አሁንም በቀድሞው አሰራር የሚሄዱ አሉ።

ይህ የህዝቡ ጥያቄ ነው። በርካታ ጥያቄዎች አሉ። በመሆኑም እምነት በሚጣልባቸው ሰዎች መመራት አለበት። በዚህ የተነሳ የሚታገሉ ሰዎች አሉ ብሎ መገመት ይቻላል። በክልሉ ውስጥ ያለውን ችግር በተወሰነ የፖሊስ ኃይል ብቻ ስለማይመለስ በተገቢው መንገድ መመለስ ይገባል። ህዝቡ የአሸባሪው ሸኔን እንቅስቃሴ እየደገፈ ነው የሚል እምነት የለኝም። ግን የጦር መሳሪያ ይዘው ከመጡበትና የሚከላከልበት ከሌለ ምንም ሊያደርግ አይችልም። በሌላ በኩል የመንግስት አካላት አሸባሪ እየመገባችሁ ነው ብለው ህዝቡን ይጠይቃሉ። በዚህ መሃል ተጎጂው ህዝብ ነው። በመሆኑም እልባት ለመስጠት ሌላ ተጨማሪ አሠራር መከተል ይገባል። የእምነት አባቶች፣ አባገዳዎች፣ ሃዳ ስንቄዎች፣ ሴቶችና ወጣቶችን ማዕከል ያደረገ ውይይት ያስፈልጋል። በዚህም ችግሩን እንዴት መፍታት ይቻላል በሚለው ላይ በጥልቀት መሥራት ይገባል። ለዚህም ስትራቴጂ መንደፍ ይገባል። መንግስትም በተደጋጋሚ የሠላም ጥሪዎችን እያደረገ ነው፤ ይህን ቢጠቀሙ መልካም ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከገዳ ሥርዓት አንፃርስ ይህን እንዴት ይመለከቱታል?**

**ዶክተር ዲማ ፡-** በገዳ ሥርዓት ይህ ፈጽሞ አይፈቀድም። ጦርነት ውስጥ ከተገባ የራሱ ህግ አለው። ይህ በንጹሃን ዜጎች ላይ የሚደረገው ነገር አግባብ አይደለም። ይህን አድርጎ የተገኘ የሚቀጣበት፣ የሚመራበትና የሚፈታበት የራሱ የሆነ ህግ አለው። መሰል ድርጊት የሚፈፅም ከህብረተሰቡ መገለል ይደርስበታል።

**አዲስ ዘመን፡-ለኦሮሞ ህዝብ ቆሜያለሁ ከሚል ቡድን በንጹሀን ላይ የሚያደርሰውን ግፍ እንዴት ይታያል?**

**ዶክተር ዲማ ፡-** መጀመሪያ እኮ ሸኔ ጥቃት የጀመረው በኦሮሞ ህዝብ ላይ ነው። ስንት ዓመት ሙሉ በኦሮሞ ህዝብ ላይ ተመሳሳይ ድርጊት ሲፈፅም አልነበረም እንዴ? እኛ እኮ እናውቃለን፤ እንሰማለን። ድርጊቱን መፈፀም የጀመረው በኦሮሞ ህዝብ ላይ ነው። አንድ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ቢኖር በማንም ህዝብ ላይ ወንጀል የሚፈፅም ሰው በራሱ ህዝብ ላይም አይተውም፤ ድርጊቱ ወንጀል ነው። ሌላ ህዝብ ላይ እጁን ያነሳ መጨረሻ ላይ ኦሮሞን ነው የሚያጠፋው።

**አዲስ ዘመን፡- በሀገራችን ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት የሚቻልበት ሰፊ ዕድል እና ሥርዓት እያለ አሸባሪው ሸኔ በህዝብና በሀገር ላይ ይህን ግፍ የሚያደርሰው ከምን የመነጨ ይመስልዎታል ?**

**ዶክተር ዲማ ፡-** ሸኔ ሲባል የከተማው ሰው የሆነ ጭራቅ ይመስለዋል። ከዚህ ህብረተሰብ የወጣ ነው ፤ አዲስ ሰው አይደለም። ምንም ከመፈለግ አይደለም። መሳሪያ ያነሳ ማንኛውም ቡድን ሥርዓት ከሌለው እንዲህ ዓይነት ወንጀል ከመፈፀም ወደ ኋላ አይልም። የተደራጀ፤ በሥነምግባር የታነፀ አንዳንዴ ፀጥታ ኃይሎችም እኮ ህገወጥ ተግባር ሊፈፅሙ ይችላሉ። መሳሪያ ያነገበ ሰው በህግ የሚመራው ለዚህ ነው። ማንኛውም የታጠቀ ቡድን ዓላማው ምንድን ነው፤ ዓላማው በመንግስት ላይ ካመፀ የመጀመሪያ ዓላማው ህዝብና መንግስትን ማጣላት ነው። አንደኛ መንግስት በሥርዓት እንዳያስተዳድር፣ ህዝብ ደግሞ ለመንግስት እንዳይገዛ በመንግስትና በህዝብ መካከል ያለውን ልዩነት ማስፋት ነው። ይህ የማንኛውም የወታደራዊ ፖለቲካ ዓላማ ያነገበ አካል ሴራ ነው። ከዚያ ደግሞ በሂደት ህዝብና ህዝብን ማጣላት ነው። በመሆኑም አሁን እየተካሄደ ያለው አንደኛ መንግስት የህዝብን ሰላም እና ደህንነት መጠበቅ አልቻለም ለማሰኘት ጭምር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሸባሪው ቡድን ዛሬም ይሁን ነገ ለኦሮሞ ህዝብ ከፍተኛ የሥጋት ምንጭ መሆኑን እንደማይቀር ብዙዎች ይናገራሉ። እርስዎ በዚህ ጉዳይ ላይ ምን ይላሉ?**

**ዶክተር ዲማ ፡-** ሸኔ ለኦሮሞ ህዝብ ይህን ያክል ከፍተኛ ስጋት ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም አሸባሪው ሸኔ በሌሎች ስትራቴጂ የሚመራ እና የራሱ ስትራቴጂ የሌለው በመሆኑ ከጀርባው ያለው ኃይል እየተዳከመ ከመጣ እሱም ቦታ አይኖረውም።

**አዲስ ዘመን፡- በአሸባሪው ሸኔ ላይ በተለያዩ የፀጥታ ሃይሎችና በህዝብ ድጋፍ ጭምር ነው ዘመቻ የተካሄደበት። ይህ በቂ ነው ይላሉ?**

**ዶክተር ዲማ ፡-** በቂ አይደለም። ከዚህ በፊት ለተለያዩ አካላት በተደጋጋሚ ተናግሬያለሁ። ይህንን በፀጥታ ኃይል ብቻ መፍታት ስለማይቻል ሌሎች ፖለቲካዊ ዘዴዎችን ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል ብዬ አስባለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- የአሸባሪው ሸኔ አሁናዊ የጥፋት መንገድ ኦነግ ለኦሮሞ ህዝብ የታገለለትን እና የከፈለውን ዋጋ ማሳነስ አይሆንም?**

**ዶክተር ዲማ ፡-** የተፈለገውም ይህ ነው። የተፈለገው ነገር ቢኖር ያንን የመሰለ ከፍተኛ መስዋዕነት ከፍሎ የኦሮሞን ህዝብ ትግል እዚህ ደረጃ ላይ ያረሰውን ኃይል ለማጠልሸት ነው። ቦታ ለማሳጣት፣ ስሙን ለማጥፋት የተደረገ ነው። ሆን ብለው ወያኔ ያደረገችው ስራ ነው። ወያኔ የኦሮሞን ህዝብ እንቅስቃሴ ለማጥፋት እና ለማሸነፍ ስላቃታት ከውስጥ ቦርቡራ ስሙንም አጠልሽታ በህዝብ ዘንድም አስጠልታ ለማጥፋት ነው ይህን ስትራቴጂ የነደፈችውና ሥራ ላይ ያዋለችው።

**አዲስ ዘመን፡- መንግስት በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ያለውን ችግር በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት እየሄደበት ያለውን የሰላም መንገድ እንዴት አገኙት?**

**ዶክተር ዲማ ነገም፡-** ጥሩ ነው! እደግፋለሁ። በሚቻለው መጠን ማንኛውንም ዓይነት ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት መሞከር ጥሩ ነው። ችግሩ ግን መንግስት ብቻ የሚፈልገው ሳይሆን ያኛውም ወገን የሚፈልገው መሆን አለበት። በጦርነት ያልተገኘውን በሰላማዊ ድርድር መፍታት ነገሮችን ማቻቻል ያስፈልጋል የሚል ነገር ይኖራል ብዬ አምናለሁ ። ነገር ግን እኔ ሰዎቹን እስከማውቃቸው ድረስ ማቻቻል የሚባል ነገር የሚያውቁ አይመስለኝም። በባህሪያቸውም ማቻቻል የሚለውን ቋንቋ አያውቁም።

**አዲስ ዘመን፡- ሌሳ ሲያስተላልፉት የሚፈልጉት መልዕክት ካለ ዕድሉን እንስጥዎ?**

**ዶክተር ዲማ ፡-** እኔ ብዙ የምለው ተጨማሪ ነገር የለም። በሰሜኑም ሆነ በየትኛም የሀገሪቱ አካባቢ እየተደረገ ያለው ጦርነት መጠኑ ቢበዛም ቢያንስም የህዝብ ህይወት እየቀጠፈ እና እያፈናቀለ ነው። የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እየጎዳ ነው። በአንዳንድ አካባቢ እርሻ እየታረሰ አይደለም። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ህዝብ ለርሃብ ተጋልጧል። ይህ የሀገሪቱንም ገፅታ እያበላሸ ነው። ስለዚህ ይህ በአስቸኳይ መፍትሄ እንዲያገኝ ቢደረግ በተቻለ መጠን ደግሞ በዴሞክራሲያዊ መንገድ መፍታት ለሀገሪቱ መፃዒ ዕድል ወሳኝ ነው። በመሆኑም የተጀመረው የእርቅ መንገድ መደገፍ የሚገባው ነው የሚል እምነት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ስለነበርዎት ቆይታ በአንባቢያን ስም እናመሰግናለን።**

**ዶክተር ዲማ ነገም፡-** እግዜር ይስጥልኝ።

# ዓለም አቀፍ

## ከሕዝባቸው መሬት የወርቅ ማዕድን ማውጣትን በድሮን ‘የገቱት’ ተሟጋቾች

በኢኳዶር የቀደምት ሕዝቦች ጥንታዊ ግዛት ላይ የወርቅ ማዕድን የማውጣትን ተግባር የተቃወሙ ሁለት ተሟጋቾች ዓለም አቀፍ የአካባቢ ጥበቃ ሽልማት አሸንፈዋል። አሌክስ ሉሲታንቴ እና አሌክሳንድራ ናርቫዝ ይባላሉ ያሸነፉትም ሽልማት ስመ ጥር የሆነውን የጎልድማን ሽልማትን ነው። ይህም ሽልማት ስር ነቀል የሆነ ለውጥን ለሚያመጡ ዘመቻዎች ወይም እንቅስቃሴዎች ዕውቅናን የሚሰጥ ነው።

በሕዝባቸው መሬት ላይ የሚደረገውን የማዕድን ቁፋሮና የማውጣት ሥራ በሰው አልባ አውሮፕላኖች (ድሮኖች) በመጠቀም መረጃዎችን ሰብስበዋል። ድሮኖችን በመጠቀም ያነሷቸም ምስሎችና ቪዲዮዎች 79 ሺህ ሄክታር የሆነው የደን ስፍራ ከማዕድን የማውጣት ሥራ እንዲጠበቅም ለማድረግ ሕጋዊ መረጃዎች ሆነው ቀርበዋል። መረጃዎቹም ድላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ወሳኝ ነበሩ።



የ29 ዓመቱ አሌክስ ሉሲታንቴ እና የ32 ዓመቷ አሌክሳንድራ ናርቫዝ 1 ሺህ 200 አባላት ያሉት የቀደምት ሕዝቦች ከሆነው የኮፋን ማሕበረሰብ ነው ትውልዳቸው። የኮፋን ማሕበረሰብ በኢኳዶር ደኖች ውስጥ ለዘመናት ኖረዋል። አሌክሳንድሪያ ‘ላ ጋርዲያ’ የተሰኘ አካባቢውን የሚጠብቁ 25 የበጎ ፈቃደኞች ቡድን መስራች እና የጥበቃ ቡድኑንም በመቀላቀል የመጀመሪያዋ ሴት ናት።

በአውሮፓውያኑ 2017 በአጓሪኮ ወንዝ ዳርቻ በመሬታቸው ላይ ማዕድን አውጪ ከባድ ማሽኖች ሲሰማሩም ለመጀመሪያ ጊዜ ያዩት የላ ጋርዲያ አባላት እንደነበሩ አሌክስ ሉሲታንቴ ለቢቢሲ ተናግሯል።

"ምርመራ ስንጀምር የኢኳዶር መንግሥት ለበርካታ ኩባንያዎች 20 የማዕድን ማውጣት ፍቃድ መስጠቱን እና 32 ተጨማሪ ለማጽደቅ እየጠበቁ መሆናቸውን ደርሰንበታል" ብሏል።

የመብት ተሟጋቹና ጠበቃ መሆን የሚፈልገው ሉሲታንቴ የኮፋን ማሕበረሰብ ቅሬታቸውን ለባለሥልጣናቱ ቢያቀርቡም ምላሽ ባለመግኘታቸው ጉዳዩን በሕግ እልባት ለማግኘት መወሰናቸውንም ይናገራል።

ሉሲታንቴ እንደሚለው ማሕበረሰቡ በሰው አልባ አውሮፕላኖች ታግዞ ያነሳቸው የአየር ላይ ምስሎች እና በግዛታቸው ላይ የተደረገውን ወረራና ጣልቃ ገብነትንም ፎቶዎቹ በዝርዝር ማሳየት በመቻላቸው ለትግላቸው ወሳኝ ሚናን ነበረው። ለአንድ ዓመት ያህልም ከዘለቀ የፍርድ ቤት ሙግት በኋላም ማሕበረሰቡ አስደናቂ ድል አስመዝግቧል።

በግዛታቸው የሚገኘው የሱኩምቢዮስ ፍርድ ቤት የኢኳዶር ባለሥልጣናት የማዕድን ፍቃዶችን በሕጋዊ መንገድ ለመስጠት የኮፋን ማሕበረሰብን አላሳወቁም፣ እንዲሁም ፍቃዳቸውንም አላገኙም ሲል ብይን አስተላልፏል። ፍርድ ቤቱ በባለሥልጣናቱ የተሰጡ ነባር ፍቃዶችን በመሰረዝ እንዲሁም በመጠባበቅ ላይ ያሉ ፈቃዶችን ውድቅ በማድረግ ማዕድን የማውጣት ሥራው እንዲቆም አዟል።

የኢኳዶር መንግሥት ይግባኝ ማለቱን ተከትሎም ፍርድ ቤቱ መሬቱ የኮፋን ማሕበረሰብ ቀደምት ግዛት መሆኑን እና በጤናማ አካባቢ መኖር እና ንጹህ ውሃ የማግኘት መብታቸው ተጥሷል በሚል የወሰነ ሲሆን ይህም ለማሕበረሰቡ ተጨማሪ ድልን አስገኝቷል።

አሌክሳንድራ ናርቫዝ ለቢቢሲ እንደተናገረችው ውሳኔው መሠረታዊና ቁልፍ የሚባል ነው፣ ምክንያቱም “ግዛታችን፣ መሬታችን ሕይወታችን ነው” ትላለች።

“ይህንን ግዛት እናውቀዋለን፤ መሬታችን ነው። የምንተላለፍበት ነው። የተቀደሱ ቦታዎችን እናውቃለን፣ ለአደን የሚሆኑ፣ እንስሳት ለመብላት የሚመጡባቸውን ቦታዎች እናውቃለን። ስፍራው ሕይወት የተሞላ ነው፤ እናም ለእኛ ሁሉ ነገራችን ነው” ትላለች።

“የኮፋን ማሕበረሰብ ያለ መሬቱ፣ ያለ ግዛቱ ኮፋን አይደለም" ስትል የጥንት ግዛታቸው ለማሕበረሰቡ ያለውን ጠቀሜታ” ትናገራለች። አሌክሳንድራ ናርቫዝ በመንግሥት ላይ ሕጋዊ ትግል ከመጀመሯ በፊት በማሕበረሰቧ ውስጥ ምን ያህል ቁርጠኛ መሆኗንና ለትግሉም የተሰጠች መሆኗን ማስመስከር ነበረባት።

“የጥበቃው አካል ወይም ላ ጋርዲያን ለመቀላቀል የመጀመሪያዋ ሴት መሆን በጣም ከባድ ነበር፤ መጀመሪያ ላይ ከወንዶችም ሆነ ከሴቶች ብዙ ትችቶች ደርሶብኛል” ትላለች። “በእኛ ማሕበረሰብ በተለምዶ ሴቶች ልጆችን እና ቤትን በመንከባከብ ቤት ውስጥ እንዲቆዩ ይደረጋል። እናም የላ ጋርዲያን አባል መሆን እንደምፈልግ ስናገር ከፍተኛ ውዝግብን ፈጠረ” በማለት ታስረዳለች።

“ነገር ግን በቁርጠኝነት ይህን ማድረግ ያለብኝ ለራሴ ብቻ ሳይሆን ለሁለቱ ሴት ልጆቼ እና በማሕበረሰባችን ላሉ ሴቶች ሁሉ ነው አልኳቸው” ስትል የነበረውን ሁኔታ ትገልጻለች። እናም በመጨረሻ በማሕበረሰቧ ውስጥ ያሉትን ጥርጣሬዎች እንዲወገዱ በማድረግና ሴቶች በባህሉ ውስጥ ያላቸው ዕውቀት ለላ ጋርዲያ ጠቃሚ መሆኑን ማሳመን ቻለች።

"ውሃ የምንቀዳው እኛ ነን፤ ለመድኃኒትነት የሚውሉ ዕፅዋትን እና የአንገት ሀብሎችን ለመስራት ዘሮችን የምንሰበስበው ሴቶች ነን። ስለዚህም ከመሬታችን፣ ከግዛታችን ጋር ጥልቅ ትስስር አለን” ትላለች። “ዓለም ድምፃችንን ሊሰማ ይገባል። እያልንም ያለነው መሬታችንን በሕይወታችን እንጠብቃለን!”

አሌክሳንድራ በቀደምት ሕዝቦች ጥበቃን ውስጥ ሴቶች እንዲሳተፉ ፈር ቀዳጅ በመሆን አምስት ተጨማሪ ሴቶች እንዲቀላቀሉ ምክንያት በመሆኗ ኩራት ይሰማታል። ለሁለት ሴት ልጆቿ በቂ ጊዜ አልሰጠኋቸውም በሚል ጸጸት የጥበቃውን ሥራ ለማቆም በተቃረበችበት ወቅትም እንድትቀጥልበት ያበረቷቷት ልጆቿ እንደሆኑ ትናገራለች።

“እማዬ፣ ጥበቃ ሂጂ! እኛ ደህና ነን፣ እኛም እንዳንቺ መሆን እንፈልጋለን። ትምህርታችንን እንደጨረስን፣ የላ ጋርዲያ መለያ ለብሰን የአንቺን ፈለግ መከተል እንፈልጋለን አሉኝ። ጥንካሬ የሰጠኝም ይህ ነው” ትላለች።

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

## ተመራቂ ተማሪዎችን ከቀጣሪ ድርጅቶች ጋር ያገናኘው አውደ ርዕይ

የብዙ ተማሪዎች የፈጠራ ውጤት መና ቀርቷል፡ ፡ተማሪዎቹ በፈጠራ ሥራዎቻቸው ለሌሎች መትረፍ ሲችሉ የሚደግፋቸው እና ከቀጣሪ ድርጅቶች ጋር የሚያገናኛቸው አጋጣሚም አናሳ ነው፡፡ ድካማቸው ፍሬ ሳያፈራ በመቅረቱ እነርሱም ይሁን ሀገሪቱ ማግኘት ያለባቸውን ጥቅም እንዳያገኙም አድርጓቸዋል፡፡



በመሆኑም ችግሩ በዚህ እንዳይቀጥል ቀጣሪ ድርጅቶችንና ተመራቂ ተማሪዎችን የሚያገናኝ የሥራ አውደ ርዕይ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ባሳለፍነው ሳምንት ተከናውኗል፡፡የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ “ዩኒቨርሲቲ ለኢንዱስትሪ” በሚል መርህ አውደ ርዕይ በከፈተበት ወቅት በትምህርት ሚኒስቴር የሳይንስና ምርምር ጉዳዮች ዳይሬክተር ጄነራል ዶክተር ሰለሞን ቢኖር እንደገለጹት፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ እውቀትና ክህሎት የዳበረ የሰው ሀብት ልማት መካሄድ ቅድሚያ ከተሰጣቸው የትኩረት መስኮች መካከል አንዱ ነው፡፡

የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት ፕሮግራሞች በመታገዝ ዘርፉን መምራት የሚችል ብቃት ያለው የሰው ኃይል ለማፍራትና የተመራማሪዎችን ቁጥር ማሳደግ የሚያስችሉ ሀገራዊ ፕሮግራሞች በመተግበር ላይ ሚናቸው የጎላ መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር ሰለሞን፤ በአሁኑ ወቅት 57 የመንግሥትና የግል ዩኒቨርሲቲዎች ያሉ ሲሆን ፤ በየዓመቱ ከ200 ሺ. በላይ ምሩቃን ቢወጡም ተገቢውን የሥራ እድል የሚያገኙት ውስን መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡

የትምህርት ጥራት ጉድለት፣ የላላ የተቋማት ትስስር ፣ የተማሪዎች ተግባር ላይ የልምምድ ውስንነት፣ አማራጭ የሥራ ዕድሎች አለመኖርና የአምራች ዘርፉ ሥራ የመፍጠር አቅም ውስን መሆን ለሥራ ዕድል መጥበብ ምክንያት እንደሆነ የሚገልጹት ዳይሬክተሩ፤ ትምህርት ሚኒስቴር ችግሩን ለመቅረፍም የተቋማት ትስስር ክፍተትን ለመቅረፍ የሚያግዝ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የኢንዱስትሪ ትስስር የሕግ ማቀፍ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ መግባቱን ያወሳሉ፡፡ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪዎችንና ሥራ ፈላጊ ምሩቃንን ለማገናኘት የሠራው ተግባር ግንባር ቀደም ሆኖ የሚጠቀስ ነው ፤ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሳይንስና ቴክኖሎጂ የተቃኘ የሰው ሀብት ልማት ማፍራት ላይ በትኩረት ሊሠሩ ይገባል በማለትም ያክላሉ፡፡

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ደረጀ እንግዳ በበኩላቸው እንዳሉት፤ በእውቀት፣ በክህሎት፣ በአመለካከትና ጊዜውን የጠበቀና አሁን ላሉበን ችግሮች መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ ምሩቃንን ማፍራት ወሳኝ ነው፡፡ በሙያቸውና በሥነ ምግባራቸው ብቁ እንዲሆኑ ዩኒቨርሲቲው ሥርዓተ ትምህርት (ካሪኩለም) በማዘጋጀት እና በመተግበር የተለያዩ ምዘናዎችን በመመዘን በቂና ብቁ መሆናቸውን



**ዶክተር ሰለሞን ቢኖር፤**


በማረጋገጥ ከኢንዱስትሪዎች ጋር ለማስተሳሰር ሲሠራ ቆይቷል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹ ለአራት እና አምስት ዓመታት ሲማሩ የሚጠበቅባቸውን በማድረግ በሙያቸው ሀገራቸውን እንዲያገለግሉ ለማብቃት በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ክህሎት እንዲኖራቸው በክፍል ውስጥ ከሚማሩት ትምህርት በተጨማሪ በተጓዳኝ እንደየሙያቸው በተለያዩ ክበባት በችሎታቸው እንዲሳተፉ በማድረግ ሙያቸውን እንዲያዳብሩም ተደርጓል፡፡

ተመራቂዎች የኮሙኒኬሽን (ተግባቦት) ክህሎታቸውን እንዲያጎለብቱና ብቁ እንዲሆኑም ተደርጓል፡፡በዩኒቨርሲቲው በሙያ ማበልጸጊያ ማዕከሉ ውስጥ ራሳቸውን ለኢንዱስተሪው ዘርፍ እንዴት ማብቃትና ማዘጋጀት እንዳለባቸው የተለያዩ ሥልጠናዎች ለአንድ ሳምንት ሰጥቷል ያሉት ዶክተር ደረጄ፤ ተመራቂ ተማሪዎች በኢንዱስትሪው ዘርፍ ውስጥ ተፈላጊና ተመራጭ በመሆናቸው ከ50 በላይ ቀጣሪ ኢንዱስትሪዎች ወደ አወደ ርዕዩ መጥተው ተመራቂ ተማሪዎች የሰሯቸውን የፈጠራ ሥራዎች በማየት እንዲቀጥሯቸው የሚያስችል የሥራ አውደ ርዕይ በዩኒቨርሲቲው ለሁለተኛ ጊዜ መካሄዱንም ያብራራሉ፡፡

እንደ ዶክተር ደረጄ ገለጻ፤ የዐውደ ርዕዩ ዓላማ ተማሪዎችን ከማስቀጠር በሻገር የተማሪዎቹ የፈጠራ ሥራ ውጤቶቹ ወደ ገበያ እንዲገቡ እና ባለሀብቶችም ተጨማሪ መዋዕለ ነዋያቸውን በማፍሰስ ወደ ምርትነት እንዲቀየር ያለው ነው፡፡ ለሌሎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እንዲረዳም ባለሀብቱ ድጋፍ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

በአጠቃላይ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የኢንዱስትሪውን ፍላጎት መሰረት በማድረግ በተለያዩ የሳይንስ፣ ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ ዘርፎች የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት ለሀገሪቱ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ዕድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ እንደሚገኝም ለማወቅ ተችሏል፡፡

# ስፖርት



## ከአቅም በታች መጫወትና የወቅቱ እግር ኳስ ውዝግቦች

**ቦጋለ አበበ**

ባለፈው አርብ የተጠናቀቀው የ2014 ቤትኪንግ የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ እስከ መጨረሻው ሳምንት ለቻምፒዮንነትና ላለመውረድ በሚደረጉ ትግሎች አጓጊ ሆኖ ተጠናቋል። ቅዱስ ጊዮርጊስ 15ኛ ድሉን ባሳካበት የመጨረሻ ሳምንት ጨዋታ በተመሳሳይ ሰዓት በተካሄዱ ጨዋታዎች የተመዘገቡ ውጤቶች መነጋገሪያነታቸው ቀጥሏል።

በተለይም በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ በፋሲል ከነማና ድሬዳዋ ከተማ መካከል በተካሄደው ተጠባቂ ጨዋታ የተመዘገበው ውጤት አወዛጋቢና አነጋጋሪ ሆኗል። ከፈረሰኞቹ በአንድ ነጥብ ርቀው ላለመውረድ የሚታገለው ድሬዳዋን የገጠሙት አፄዎቹ የቻምፒዮንነት እድላቸውን ጨዋታውን በማሸነፍ የፈረሰኞቹን ነጥብ መጣል መጠባበቅ ነበረባቸው። በዚህም አፄዎቹ ጨዋታው ሊጠናቀቅ 13 ደቂቃ እስኪቀረው ድረስ ሁለት ለዜሮ መምራት ቢችሉም በቀሪ ደቂቃዎች 2ለ3 መሸነፋቸው የስፖርት ቤተሰቡን አስደንግጧል። በዚህ ጨዋታ አፄዎቹ ተፎካካሪያቸው ቅዱስ ጊዮርጊስ ቻምፒዮን ለመሆን የሚያስችለውን ውጤት በእጁ እንዳስገባ አረጋግጠው ሆን ብለው ለተጋጣሚያቸው ድሬዳዋ ውጤት በመልቀቅ ከመውረድ ታድገውታል የሚል ትችት እየተሰነዘረባቸው ይገኛል። ይህን ወቀሳ የሚያቀርቡ የስፖርት ቤተሰቦች በምንም መመዘኛ የሁለቱ ቡድኖች(ድሬዳዋና ፋሲል) ያላቸው ወቅታዊ አቋምና አቅም እንደማይገናኝ ይሞግታሉ።

ለዚህም ማሳያነት በእኩል 29 ጨዋታዎች 62 ነጥብና 30 ነጥብ የሰበሰቡ ክለቦች በአቅም ደረጃ ሊገናኙ እንደማይችሉ ያስቀምጣሉ። በመጀመሪያ ዙር ፋሲል ከነማ ድሬዳዋን 4ለ0 መርታቱን በማስታወስም በጨዋታው ሆን ብሎ ውጤት የማስቀየር ሽፍጥ መሰራቱን ይከራከራሉ። ይህን ሙግት የሚያነሱ ወገኖች ተፈፀመ ለሚሉት ውጤት ሆን ብሎ የማስቀየር ውንጀላ ተጨባጭ ማስረጃ ማቅረብ ባይችሉም ውጤቱ ሊጉን በቅርበት ለሚከታተሉና ገለልተኛ የሆኑ የስፖርት ቤተሰቦች ጭምር ልባቸው እንዳልተቀበለው አልሸሸጉም።

ከጨዋታው አስቀድሞ የአፄዎቹን የቻምፒዮንነት ተስፋ ይዞ ወደ ሜዳ የገባው አዲስ አበባ ከተማ ለቅዱስ ጊዮርጊስ ውጤት ለቋል ብለው ካሰቡ አፄዎቹ ለድሬዳዋ በተመሳሳይ ውጤት እንደሚለቁ አሉባልታዎች ሲነዙ ነበር። በጨዋታዎቹ የተፈጠረውና የተመዘገበውም ይሄው መሆኑን ለመናገር ያልሸሸጉ ገለልተኛ የስፖርት ቤተሰቦችም አልጠፉም። አፄዎቹ ካቻምና ዋንጫ የማንሳት የተሻለ እድል በነበራቸው ሰዓት ስሁል ሽረ ለመቀለ 70 እንደርታ ውጤት በመልቀቁ ተመሳሳይ በደል ደርሶባቸው እንደነበር የሚያስታውሱ የእግር ኳስ ወዳጆች ተመሳሳይ ነገር መፈጠር እንዳልነበረበት ወቀሳቸውን ይሰነዝራሉ። በዚህ መካከል ከሊጉ የወረደው የአዲስ አበባ ከተማ ደጋፊዎች ደረሰብን ለሚሉት በደል አፄዎቹ ተጠያቂ መሆናቸውን ከመናገር አልተቆጠቡም። አሰልጣኝ ጳውሎስ ጌታቸውም «በዚህ አይነት መንገድ ከፕሪሚየር ሊጉ መውረድ ወንጀል ነው፣ ይሄ የሀዘኔ ቀን ነው» ብለው መናገራቸው ጨዋታዎቹ በጤናማ መንገድ አለመጠናቀቃቸውን እንደሚጠቁም በርካቶች በማህበራዊ ሚዲያው አስተያየት ሲሰጡበት ለመታዘብ ተችሏል። በርግጥ እኚህ አሰልጣኝም ቢሆኑ ላለመውረድ የሚጫወት ቡድን ይዘው «ለክብር ነው የምንጫወተው» ማለታቸውና በወሳኝ ሰዓት ለተጫዋቾቻቸው ዕረፍት መስጠታቸው ለፈረሰኞቹ ውጤት እንደለቀቁ ማሳያ ተደርገው የሚቀርቡ ክርክሮችም በሌላ ወገን ሲነሱ ታይተዋል።

በእለቱ በተመሳሳይ ሰዓት በተካሄደው ሶስተኛ ጨዋታ ሀዋሳ ከተማ መርሃግብር ለማሟላትና ደረጃውን ከፍ አድርጎ ለማጠናቀቅ ወደ ሜዳ ሲገባ በተቃራኒው አዳማ ከተማ ላለመውረድ የመጨረሻውን ፍልሚያ ሊያደርግ ወደ ሜዳ እንደ ገባ ይታወቃል። አዳማ ከተማ በቀድሞ የአዳማ አሰልጣኝ ዘርዓይ ሙሉ የሚሰለጥነው ሀዋሳን ሊያሸንፍ ይችላል ተብሎ ቢገመት እንኳን በጨዋታው መላቀቅ አልነበረም ወይ የሚለው የብዙዎች ጥያቄ ነው።

የፕሪሚየር ሊጉ አክሲዮን ማህበር እነዚህን ጉዳዮች አጣርቶ ምላሽ ይሰጣል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን በዋናነት በቀጣይ ዓመታት እግር ኳሱ በንፁህ ስፖርታዊ ጨዋነትና ፍትሃዊ ፉክክር እንዲቀጥል ክለቦች ከአቅም በታች መጫወት ወይም መላቀቅ እንዳይኖር ቀደም ብሎ ከክለቦች ጋር በመነጋገር አንድ ወጥ ሕግና ደንብ በማዘጋጀት የመግባቢያ ሰነድ መፈራረም እንዳለባቸው ከዘንድሮው የመጨረሻ መርሃ ግብር ጨዋታዎች ትምህርት መውሰድ እንዳለበት የብዙዎች እምነት ነው።

ከአቅም በታች የመጫወት ጉዳይ ለአገሪቱ እግር ኳስ ሌላ አሳሳቢ ችግር መሆኑ ቢታመንም ከሊጉ የወረዱ ክለቦችን በተመለከተ ሁሉንም የስፖርት ቤተሰብ በሚባል ደረጃ የሚያስማሙ እውነታዎች እንዳሉ ግን መካድ አይቻልም። ኢትዮጵያ ላይ በችሎታ ደረጃ ደካማ የሚባል ክለብ የለም፣ ነገር ግን ደካማ አመራር የሌለበት ክለብ ፈልጎ ማግኘት አዳጋች ነው። የወረዱትን ክለቦች ለአብነት ብንመለከት እንኳን በእግር ኳሳዊው ፉክክር ተመጣጣኝ ቢሆኑም አመራሮቻቸው ደመወዝ ባለመክፈል፣ የስራ ቦታን አመቺ ባለማድረግ የክለቦቹን ስነልቦና በመግደል እንዲወርዱ ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳላቸው መሸሸግ አያስፈልግም።

በዚህ ላይ አሁን ካሉት ክለቦች አብዛኞቹ እራሳቸውን የክለብ አወቃቀር ውስጥ ለማስገባት እየሞከሩ አለመሆኑ ደሞ ለአገሪቱ እግር ኳስ ሌላኛው እራስ ምታት መሆኑ መዘንጋት የለበትም። ክለቦች የራሳቸውን ገቢ ለማመንጨት የግድ ፕሮፌሽናል የክለብ አመራር ሊኖር ይገባል። ብዙዎቹ ለማለት በሚያስደፍር ሁኔታ ግን የኢትዮጵያ ክለብ አመራሮች ዳኞችን በጥቅም ሲያማልሉ እንጂ አደረጃጀታቸውን ለመቀየር ያላቸው ፍላጎት እምብዛም መሆኑ ሚስጥር አይደለም። የሊግ ካምፓኒውም ከአቅም በታች የመጫወት ጉዳይን ብቻ ሳይሆን አንዳንድ አስገዳጅ ህጎችን እያወጣ የተበላሸውን ኢ. እግር ኳሳዊ አካሄድ እንዲያከትም ጉልህ ሚና ሊጫወት እንደሚገባው ይታመናል።


## የሀገር ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ

**የጨረታ ቁጥር ሙሲፋ/RE-15/2014**

በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ለሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ አገልግሎት የሚውል የወርክሾፕ አነስተኛ ማሽነሪ ዕቃዎች በጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል::

ስለዚህ ሕጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን ግብር የከፈሉና የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ ተጫራቾች የማይመለስ ብር 115.00 ከነቫቱ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን በአዲስ አበባ በቅሎ ቤት አካባቢ ጋራድ ህንፃ ቢሮ ቁጥር 432-3-8 ከሚገኘው የግዥ መምሪያ ቢሮ እየቀረቡ መግዛት ይችላሉ:: ተጫራቾች ለጨረታ የቀረቡትን ጠቅላላ ብር 2% የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን ሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ ስም በባንክ በተረጋገጠ ሲ.ፒ.ኦ /CPO/ ከቴክኒክ ዶክመንቶቹ ጋር በማያያዝ ይህ ጨረታ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ ሐምሌ 23 ቀን 2014 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ድረስ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ የጨረታ ሰነዳቸውን አዲስ አበባ በሚገኘው በግዥ መምሪያ ቢሮ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል::

ጨረታው በዕለቱ ሐምሌ 23 ቀን 2014 ዓ.ም ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት በግዥ መምሪያ ቢሮ ይከፈታል::

ፋብሪካው ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የጠበቀ ነው::

ስልክ 0114420216
ፋክስ 0114420688
አዲስ አበባ

**በኬሚካል ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን**
**የሙገር ሲሚንቶ ፋብሪካ**

## ማስታወቂያ

ሸባባው አያና ማርብል በቤ/ጉ/ክ/መንግስት መተከል ዞን ቡለን ወረዳ ጎንጎ ቀበሌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ የእምነበረድ ማዕድን ምርመራ ሥራ ለማካሄድ በቀን 15/10/2012 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መ/ቤታችንን ጠይቀዋል::

በመሆኑም በሚመለከተው ጂኦግራፊክ ኮርድኔት ክልል፤

1. $36^{0}$ 02' 45.7041" E $10^{0}$ 22' 39.6908"N
2. $36^{0}$ 02' 43.1968" E $10^{0}$ 22' 30.3673"N"
3. $36^{0}$ 02' 21.5919" E $10^{0}$ 22 36.5745" N
4. $36^{0}$ 02' 24.2331"E $10^{0}$ 22 45.6066." N

ውስጥ በሚገኘው ቦታዎች ላይ ይገባኛል የሚል ቢኖር ይህ ማስታወቂያ በወጣ በሰባት ተከታታይ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ከነምክንያቱ ለኤጀንሲያችን እንዲያቀርቡ እናሳስባለን::

**የማዕድን ሀብት ልማት ኤጀንሲ**

## የስብሰባ ጥሪ

የብሉ ናይል ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች አክሲዮን ማህበር ሰባተኛው መደበኛና አምስተኛው ድንገተኛ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ አጀንዳዎች

| ተ.ቁ | አጀንዳ |
|---|---|
| 1 | የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ አጀንዳዎችን ማጽደቅ |
| 2 | የ2013/2014 በጀት ዓመት የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ማዳመጥ |
| 3 | የ2013/2014 በጀት ዓመት የኦዲተሮች ሪፖርት ማዳመጥ |
| 4 | በተመረጠው የአስመራጭ ኮሚቴ ኃላፊነት የዳይሬክተሮች ቦርድ ምርጫ ማካሄድ |
| 5 | የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድን ማጽደቅ |
| 6 | የመደበኛ ስብሰባ ቃለ ጉባዔን ማጽደቅ |
| 7 | የድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ አጀንዳዎችን ማጽደቅ |
| 8 | መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻል |
| 9 | የድንገተኛ ስብሰባ ቃለ ጉባዔን ማጽደቅ |

**ማሳሰቢያ፤**

1. የስብሰባ ቦታው በማህበሩ ዋና ቢሮ የካ ክ/ከተማ ከካራ 1ኪ.ሜትር ወደ የካአባዶ በሚወስደው ዋናው አስፋልት መንገድ አዞን ት/ቤት ፊት ለፊት በሚገኘው ግቢ ውስጥ ነው:: ሆኖም ግን በግንባታው መስፋፋት የተነሳ የመሰብሰቢያው ግቢ ቦታ ለመሰብሰቢያ የሚጠበን መሆኑ በቦርዱ ከተረጋገጠ ቦርዱ በጋዜጣ፣ በኤስ.ኤም.ኤስ፣ በራዲዮ ቀድሞ የተቀየረውን አዲስ የመሰብሰቢያ ቦታና ቀን ለባለአክሲዮኖች ያሳውቃል::
2. የስብሰባው ቀን ጥቅምት 20/2015 ዓ.ም፣ ስብሰባው የሚጀምርበት ሰዓት ከጠዋቱ 2፡30 ተጀምሮ 6፡00 ሰዓት ላይ ይጠናቀቃል::
3. የተሰብሳቢ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎች ማንነትን የሚገልፅ የታደሰ መታወቂያ፣ ፓስፖርት፣ መንጃ ፈቃድ፣ የገዙበትን ደረሰኝ ወይም ሰርተፊኬት ይዘው መምጣት ይኖርብዎታል::
4. በስብሰባው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ከስብሰባው ሦስት ቀናት በፊት በአ/ማህበሩ ዋናው ቢሮ በመቅረብ የውክልና ቅጽ ሞልተው መፈረም ይኖርባቸዋል::

**ሰበስጠ መረጃ :**

**በአ/ማህበሩ ዋናው ቢሮ በመገኘት ወይም በስልክ ቁጥር፡- +251 11- 872 3332 /33/ 34 በመደወል መረጃ መውሰድ ይቻላል::**

**የብሉ ናይል ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ሥራዎች አ.ማ**